የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት

ሞጁል አንድ

አዘጋጆች፡- ተገኔ ጌታነህ
ከድር መሀመድ

የፍትህ አካላት ባለሞያዎች የስልጠና ማእከል
የወረዳ ዳኞች እና ዐ/ሕግ ስልጠና ፕሮግራም

ነሐሴ 2000
አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

አህጽሮተ ቃላት ii

መግቢያ 1-2

1. ትርጉምና ዓላማ 3-6

2. የወንጀል ፍትህ ሂደት አጀማመር እና ስለ ሚkረጥበት ሁኔታ 7-15

2.1. የወንጀል ፍትህ ሂደት አጀማመር 7-12

2.1.1. የወንጀል ክስ(Accusation) እና የግል ተበዳይ አቤቱታ(Complaint) 7-11

2.1.2. የእጅ ከፍንጅ ወንጀል አፈጻጸም 11-12

2.2. የወንጀል ፍትህ ሂደት ስለሚkረጥበት ሁኔታ 12-14

3. የፖሊስ ምርመራ 16-29

3.1.የማስረጃ አሰባሰብ 17

3.2. መያዝ (Arrest) 18-20

3.2.1. በፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለ መያዝ 18-19

3.2.2. ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለ መያዝ 19-20

3.3. የዕምነት ቃል 20-21

3.4. መበርበር ና መያዝ (Search and Seizure) 22-25

3.4.1. በፍ/ቤት ትዕዛዝ መበርበር ና መያዝ 22-24

3.4.2. ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ መበርበር ና መያዝ 24-25

3.5. ከተጠርጣሪ አካል ላይ የሚወሰድ ማስረጃ 25-27

4. ጊዜ ቀጠሮ 30-34

5. ቀዳሚ ምርመራ 35-38

6. በዐቃቢ ሕግ ክስ የማይቀርብበት ሁኔታ እና የክስ አመሰራረት 39-47

6.1. በዐ/ህግ ክስ የማይቀርብባቸው ሁኔታዎች 39-41

6.2. ክስን ማቅረብ 42-46

ዋቢ ጽሁፎች 48

አህጽሮተ ቃላት

1. የወንጀል ህግ አንቀጽ	የወ/ሕ/አ
2. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት ቁጥር	የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ

መግቢያ

ወንጀል የአንድን ማኅበረተሰብ ህልውና አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግር ነው። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ወንጀል ተብለው ተለይተው በሕግ ላይ የተመለከቱ ተግባራት ተፈፅመው ሲገኙ ተጠያቂነት ሊከተል ይገባል። አጥፊውን የመለየት አካሄድ ያለ አግባብ ያላጠፋን ሰው እንዲጠየቅ እንዳያደርግ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ነው ንፁህ ሰው ያለጥፋቱ ከሚቀጣ ዘጠና ዘጠኝ ወንጀል የሠራ በነፃ ቢለቀቅ ይሻላል የሚባለው።

የወንጀል ሕግ በሥራ ላይ ሲውል የማኅበረሰቡ ጥቅም እንዲጠበቅ ና የዜጎች ሰብዓዊ መብትም እንዳይጣስ ማድረግ የግድ ያስፈልጋል። ይህንን ለማረጋገጥ የዓለም ሃገራት ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው የሕግ ሥርዓት አበጅተው እየሠሩ ይገኛሉ። በተመሣሣይ በሃገራችንም የወንጀል ሕግ በሥራ ላይ የሚውልበት ሕገ መንግሥቱን መሠረት ያደረገ ሕጋዊ ሥርዓት ተዘርግቶ በተግባር ላይ እየዋለ ነው። የዚህ ጽሑፍ ዓላማም ይኸው ሕጋዊ ሥርዓት እና አተገባበሩ ምን እንደሚመስል ለሥልጠና በሚያግዝ መልኩ ማስቀመጥ ነው።

የሥነ ሥርዓት ሕግ በራሱ ተግባር ተኮር ስለሆነ ና የሥልጠና ዓላማም ሠልጣኞችን ለተግባር ማብቃት በመሆኑ ጽሑፉ የሕጉ አተገባበር ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል። በተጨባጭም ሕጉ ሥራ ላይ ሲውል የሚያጋጥሙና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ተካተዋል። ይሁንና ሕጉን ለመረዳት ዕንሰ ሃሳቦችን ማብራራት የግድ አስፈላጊ በመሆኑ በቅድሚያ እንዲታዩ የተደረገ ሲሆን በጽሑፉ ውስጥም አስፈላጊነታቸው እየታየ እንዲገቡ ተደርጓል።

የወንጀል ሕግ በሥራ ላይ የሚውለው ወንጀል ተብሎ በህግ የተደነገገ ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ ነው። በዚህ መሠረት ወንጀል ተፈፅሞ ሲገኝ የፖሊስ ምርመራ ማከናወን፣ በዐቃቤ ሕግ ክስ መመሥረት፣ በፍ/ቤት ጉዳዩ እንዲታይ ማድረግ፣ ቅጣት መወሰን፣ ቅጣቱን ማስፈፀም እና በሚሰጥ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብን የመሣሰሉ ወሣኝ ሂደቶችን የሚያልፍ በመሆኑ የጉዳዮችን አካሄድ በተከተለ መልኩ ሕጉና አተገባበሩ ምን እንደሚመስል በጽሑፉ ሽፋን እንዲያገኝ ተደርጓል። በመሆኑም የወንጀል ፍትሕ ሂደት

እንዴት ተጀምሮ እንደሚጠናቀቅ ደረጃ በደረጃ የምንመለከተው ሲሆን ለአቀራረብ እንዲያመች በሶስት ሞጁሎች ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡

በመጀመሪያው ሞጁል ውስጥ ጽንሰ ሀሳብ፣ ወንጀል ክስ አጀማመር ና የሚቋረጥበት መንገድ፣ የፖሊስ ምርመራ፣ ጊዜ ቀጠሮ፣ ቀዳሚ ምርመራ እና በዐ/ህግ ክሰ መዝጋት ና ክስ መመስረት ተካተዋል፡፡ ዋስተና በየትኛውም ደረጃ ሊታይ የሚችልም በመሆኑ በመጨረሻው ክፍል ውስጥ እነዲገባ ተደርጎዋል፡፡ በሁለተኛው ሞጁል በዋነኛነት በፍ/ቤት የክስ መስማት ሂደት የተዳሰሰ ሲሆን ተያይዘው የፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን ና በፍ/ቤት የቅድመ ክስ መስማት ሂደት ቦታ ተሰጥቶዋቸዋል፡፡ በመጨረሻው ሞጁል ዋስትና፣ ከመደበኛው የክስ መስማት ሂደት በተለየ ሥነ ሥርዐት የሚሥተናገዱ ጉዳዮች፣ ይግባኝ፣ የቅጣት አስተዳደር ና አመክሮ ሽፋን አግኝተዋል፡፡ ይህንኑ ክፍፍል መሰረት በማድረግ በዚህኛው ቀዳሚ ሞጁል ውስጥ የተካተቱት ነጥቦች ቀርበዋል፡፡

1. ትርጉም እና ዓላማ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ሠልጣኞች ይህንን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፦

- **የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ምን እንደሆነ ይተነትናሉ፤**
- **ሕገ መንግሥቱ እና የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ያላቸውን ግንኙነት አውቀው ለተግባራዊነታቸው በዕናት ይሠራሉ፤**
- **በሀገራችን ከወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ህጎች ያብራራሉ፡፡**

በዚህ ክፍል ውስጥ ዋና ዋና ፅንሰ ሃሳቦች ምን እንደሆኑ በቅድሚያ መታወቅ ስላለባቸው እንዲብራሩ ይደረጋሉ፡፡ በዚሁ መሰረት ራሱ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ምንድነው የሚለው ይዳሰሳል፡፡ ከዚህ ሌላ ማንኛውም በአንድ አገር ያለ ሕግ የሕጎች ሁሉ የበላይ ከሆነ ከሕገ መንግሥት አንፃር መታየት ስላለበት የሥነ ሥርዓት ሕጉና ሕገ መንግሥቱ ያላቸው ትስስርም አብሮ እንዲታይ ይደረጋል፡፡

በታዋቂው ብላክስ የሕግ መዝገበ ቃላት ትርጓሜ መሠረት የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት የሚከተለው ፍቺ ተሠጥቶታል፦

> *Criminal procedure means the rules governing the mechanisms under which cri mes are investigated, prosecuted, adjudicated, and punished. It includes the pr otection of accused persons' constitutional rights.*

ሕጎች በአጠቃላይ ከይዘታቸው አንፃር ዋና ሕጎች (substative lasws) **እና ቅፅል ሕጎች** (adjective laws) **ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ መሠረታዊ ሕጎች የሚባሉት መብት፣ ግዴታ እና ተጠያቂነትን**(liability) **የሚመለከቱ ሲሆን፣ ቅፅል ሕጎች ደግሞ እነዚህ በሕግ ላይ የተመለከቱ መብት፣ ግዴታና ተጠያቂነት በአግባቡ በተግባር ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ የሚገዙ ናቸው፡፡ ቅፅል ሕጎች እንደገና የሥነ ሥርዓት** (procedural)

እና የማስረጃ (evidence) በመባል በሁለት ይከፈላሉ። ከላይ ስለ ወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ከተሰጠው ትርጓሜ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ወንጀልን የሚያቋቁሙ መስፈርቶችን የሚደነግገው ዋናው የወንጀል ሕግን በሥራ ላይ የሚያውለው የሥነ ሥርዓት ሕጉ ነው። ወንጀል ተፈፀመ ከተባለ በዋነኛነት በፖሊስ ምርመራ ይጣራል፤ በቂ ማስረጃ ከተገኘ በዐቃቤ ሕግ ክስ ይመሠረታል፤ ከዚያም ጉዳዩ በፍ/ቤት ታይቶ ጥፋቱ ከተረጋገጠ ተገቢው ቅጣት እንዲወሰን ይደረጋል።

ወንጀል የሠራ እንዲጠየቅ ማድረግ የማጎበረሰቡን ጥቅም የሚያስጠብቅ ቢሆንም ሂደቱ አጠፋ የተባለውን ሰው ሰብዓዊ መብቶች የሚጥስ መሆን የለበትም። የማጎበረሰቡን ጥቅምና የግለሰቡን መብት በተቻለ መጠን በሚያስታርቅ መልኩ ሕጉ ሥራ ላይ መዋል አለበት። የሥነ ሥርዓት ሕጉ ዋና ዓላማም ይህ ዕውን እንዲሆን ማድረግ ነው።

ወንጀል ፈፃሚን ለይቶ አጣርቶ የማግኘት ሂደት በእጅጉ ከዜጎች ሰብዓዊ መብቶች ጋር የተቆራኘ ነው። የሰብዓዊ መብቶች መከበር ደግሞ ዴሞክራሲ እና መልካም አስተዳደር በሠፈነበት አገር ወሣኝ በመሆኑ በቂ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል። ሃገራት የጉዳዩን አሳሳቢነት ከግምት በማስገባት ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ጭምር ይሰጡታል። ከላይ ስለወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ከተሰጠው ፍቺም ለማረጋጥ እንደሚቻለው በሂደቱ ምንጊዜም ቢሆን የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር እንዳለባቸው ነው። በመሆኑም የወንጀል ህግን ስራ ላይ ማዋል እና በወንጀል የተከሰሰን ሰው ሰብአዊ መብት ማክበር የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው።

በሃገራችን ለግማሽ ምዕተ ዓመት ያክል በሥራ ላይ የነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ተሽሮ በአዲስ የወንጀል ሕግ ተተክቷል። ነገር ግን የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓቱ የተሻረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን በሥራ ላይ ለማዋል ወጥቶ በሥራ ላይ የነበረው አሁንም ድረስ ፀንቶ ያለ ሲሆን በቅርቡ ተሻሽሎ ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። ይህ ነባሩ ህግ ዝርዝር ጉዳዮችን የላካተተ በመሆኑ ለሚነሱ የተለያዩ ጥያቄዎች ከህጉ ምላሽ ማግኘት ከባድ ነው። ህጉ ሲሻሻል እነዚህ ክፍተቶች መሞላት አለባቸው። እስከዚያው ያለውን ህግ በአግባቡ ተርጉሞ ስራ ላይ ማዋል ተገቢ ነው። ይኸው ህግ ያካታቸው በርካታ ጠቃሚ እና ዘመናዊ ድንጋጌዎች ለረዥም ጊዜ ባለመተግበራቸው

የወንጀል ፍትህ ይጎተት እንደነበረ ይታወቃል። በመሆኑም ክፍተቶች ቢኖሩትም ያለውን ህግ እንዳለ ስራ ላይ የማዋሉ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተጨማሪ ግን ሌሎች የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ሕጎችን ያካተቱ ሕጎችም የሚገኙ ሲሆን ለአብነት ያክል የወነጀል ህጉ፣ አደገኛ ቦዘኔነትን ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 384/96 እና የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥረዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 ተጠቃሾች ናቸው።

ከዚህ ሌላ ማይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አንድ ሦስተኛውን ቦታ የሚሰጠውና የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት መሰረታዊ ድንጋጌዎችን ያካተተው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት ነው። በሕገ መንግሥቱ እንደሌሎች ሃገሮች ሁሉ በወንጀል ተጠርጥረው የተያዙና የታሰሩ ሰዎች ጉዳያቸው ሊስተናገድበት ስለሚገባበት ሁኔታ እና ስለ ሰብዓዊ መብታቸው አጠባበቅ ድንጋጌዎች ይገኛሉ። ዐ/ህግ እና ዳኞች ሁልጊዜ አግባብነት ያላቸውን የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ተርጉመው ስራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ሲያደርጉ ግን በህገ መንግስቱ ለፌዴሬሽን ም/ቤት የተሰጠውን ሰልጣን ማክበር አለባቸው። ይህ እነደተጠበቀ ሆኖ ህገ መንግሰቱ መተግበር አለበት። ለምሳሌ በህገ መንግሰቱ አንቀጽ 19/5 ስር በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም(inadmissible):: በተጨባጭ ከሚያጋጥሙ ጉዳዮች አንጻር ታይቶ ማስረጃው በማስገደድ የተገኘ ነው ወየስ አይደለም? ተብሎ በዐ/ህግ ና ዳኞች መወሰን አለበት።

በሕገ መንግሥቱ፣ በወንጀል ሕጉ ና በወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕጎቹ ተደንግገው የሚገኙት ሥነ ሥርዓት ነክ ድንጋጌዎች ብቻ ማይሆኑ የወንጀል ማስረጃን ጭምር የሚመለከቱ ናቸው። ማስረጃን በተመለከተ ሀገራችን የሲቪል ሎው የህግ ሥረዓትን ከሚከተሉት ሃገራት ተርታ ስለምትመደብ የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓትን እንደሚከተሉ ሃገራት ራሱን የቻለ የማስረጃ ሕግ የላትም። ከማስረጃ ጋር የተየያዙ ድንጋጌዎች በተለያዩ ሕጎች ውስጥ ተካተው ነው የሚገኙት።

ለማጠቃለል ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በሃገራችን ያሉት የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች በሁለት ዋና ዋና ክፍል ሊመደቡ ይችላሉ። እነርሱም የሕገ መንግሥት

መሠረት ያላቸው የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች (constitutional criminal procedure rules) እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓትን ጨምሮ በሌሎች ሕጎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች (statutory criminal procedure rules) ናቸው::

የመወያያ ነጥቦች

1. የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ምንድነው ?

2. የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ና የአንድ ሃገር ሕገ መንግሥትን ምን ያገናኛቸዋል?

3. በሃገራችን የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን በየትኞቹ ሕጎች ውስጥ እናገኛቸዋለን?

4. የወንጀል ህግ ማስረጃስ በየትኞቹ ሕጎች ውስጥ ይገኛል?

5. ህገ መንግስታዊ መሰረት ያላቸውን የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች ተርጉሞ ስራ ላይ በማዋል ረገድ ከፀ/ህግ እና ዳኞች ምን ይጠበቃል? በዚህ ረገድ ለፌዴሬሽን ም/ቤት ህገ መንግስቱን ለመተርጎም ከተሰጠው ስልጣን ጋር እንዴት ያዩታል?

2. የወንጀል ፍትሕ ሂደት አጀማመር እና ስለ ሚቋረጥበት ሁኔታ

የሚጠበቁ ውጤቶች፤

ሠልጣኞች ይህንን የሥልጠናውን ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ፦

- **የወንጀል ፍትሕ ሂደት እንዲጀመር የሚያስፈልጉ ሕጋዊ ቅድመ ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ያስረዳሉ፤**
- **የወንጀል ፍትሕ ሂደቱ አንድ ጊዜ ከተጀመረ በኋላ የሚቋረጥባቸውን ሕጋዊ መንገዶች አውቀው በሥራ ላይ ያውላሉ፤**

የወንጀል ሕግ ሲጣስ የጉዳዩ መታየት እንዴት እንደሚጀመር በዚህ ክፍል ይታያል። የወንጀል ፍትሕ ሂደት አንድ ጉዞ ከተጀመረ በኋላ በሕግ ላይ የተቀመጠውን ሥርዓት ተከትሎ ሊጠናቀቅ ሲችል ሊቋረጥ የሚችልባቸውም መንገዶች ተካተዋል።

2.1. የወንጀል ፍትሕ ሂደት አጀማመር

የወንጀል ሕግ ጥሰት ሲኖር ጉዳዩ በሚመለከተው የፍትሕ አካል ታውቆ የፖሊስ የምርመራ ሥራ የሚጀመርበት የራሱ የሆነ ሕጋዊ ሥርዓት አለው። ይህ አካሄድ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። እነሱም የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ ማቅረብ እና የእጅ ከፍንጅ የወንጀል አፈፃፀም ሁኔታ መኖር ናቸው። እነዚህ ሁለት መንገዶች የየራሣቸው የተለያየ ባህሪ ስላላቸው ተለያይተው ይታያሉ።

2.1.1. የወንጀል ክስ(Accusation) እና የግል ተበዳይ አቤቱታ(Complaint)

ማንኛውም ሰው ወንጀል ሲፈፀም ካየ ወይም ወንጀሉ ሲሠራ ያልተመለከተም ቢሆን መሠራቱን ካወቀ ለሚመለከተው የፍትሕ አካል የማስታወቅ መብት አለው። በመሠረቱ ሁኔታውን ለፍትሕ አካላት ማስታወቅ ግዴታ አይደለም። ነገር ግን አለማስታወቁ በግለሰብ ና ማኅበረሰብ ህልውና ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ከባድ አደጋ በማገናዘብ በልዩ ሁኔታ ማስታወቅ እንደ ግዴታ በሕግ ላይ ሊቀመጥ ይችላል። ለአብነት ያክል የወ/ሕ/አ 254፣ 335 እና 443 እንዲሁም የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና

አሠራሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 60/89 /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 81-82 መጥቀስ ይቻላል::

በሃገራችን ወንጀሎች በሁለት ዋና ዋና መደቦች በሕግ አስከባሪ/ዐቃቤ ሕግ የሚቀርቡ /የወንጀል ክስ ተብለው የሚታወቁ/ እና በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ተብለው ይከፈላሉ /የወ/ሕ/አ 211/ ይህ በወንጀል ሕጉ ላይ የተደረገው ክፍፍል ወንጀሎቹ ተፈፀሙ ከተባለ በኋላ ጉዳዮቹ የሚስተናገዱበት ሥርዓት ላይ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል::

ወንጀል የሚባሉ ተግባራት የኅብረተሰብን ሕልውና ይነስም ይብዛ የሚፈታተኑ ሠላምና መረጋጋትን የሚያደፈርሱ በመሆናቸው በመሠረቱ ተፈፅመው ሲገኙ ጉዳዩ በፖሊስ ተጣርቶ አጠፋ የተባለውን ለማስጠየቅ የሚያስችል በቂ ማስረጃ ካለ በዐቃቤ ሕግ ለፍ/ቤት ክስ ቀርቦ መታየት አለበት:: ይሁንና አንዳንድ ጉዳዮች ከማኅበረሰባዊ ገፅታቸው ይልቅ ግላዊ ባህሪያቸው ይጐላል:: ስድብ፣ ዛቻና እጅ ዕልፈት የመሣሠሉ ቀላል ጉዳዮች በቀጥታ የሚጐዱት በደሉ የደረሰበትን ነው:: ተበዳይ ወገን ፍትሕ ጠ ይቆ ሕጋዊ ምላሽ ካላገኘ የራሱን ዕርምጃ ወደ መውሰድ ስለሚያመራ ጉዳቱ ለሁሉም የኅበረተሰቡ አካል ነው:: ሌላውም ተመሣሣይ በደል ሲደርስብኝ መፍትሔ አላገኝም ብሎ ካሰበ የበቀል ተግባር ውስጥ ሊገባ ስለሚችል አደጋው የከፋ ነው:: እዚህ ጋር መታየት ያለበት በእንደዚህ ዓይነት ቀላል ጉዳዮች የተበደለው ወገን መፋረድ ካልፈለገ አጠፋ የተባለውን ሰው እንዲጠየቅ ማድረግ ምን ዓይነት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ ይኖረዋል? የሚለው ነው:: በዚህ ሁኔታ አጠፋ የተባለውን መቅጣቱ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል:: ለዚህም ይመስላል በወንጀል ሕጋችን በሕግ አውጪው ቀላል ተብለው የተገመቱ የወንጀል ተግባራትን በተመለከተ ተጐዳ የተባለው ሰው ክስ ካላቀረበ በስተቀር በወንጀል አያስጠይቁም ተብሎ የተደነገገው::

በመርህ ደረጃ ማንኛውም ወንጀል በሕግ አስከባሪ የሚቀርብ ነው:: የተበደለው ወገን ክሱን አልፈልግም ቢልም ጉዳዩ ሕዝብን የሚመለከት በመሆኑ በፍትሕ አካላት መስተናገዱ ይቀጥላል:: ነገር ግን በሕግ አውጪው የወንጀሉ ባህሪ እና ክብደት ከግምት ገብቶ በልዩ ሁኔታ በግልፅ ተለይቶ የተበደለው ወገን ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ክስ ማቅረብ መፈለግ እንደ ቅድመ ሁኔታ (condition precedent) ከተቀመጠ ይህ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ሣይሟላ ክስ ማቅረብ አይቻልም::

በወንጀል ሕጋችን ውስጥ በግል አቤቱታ የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች በተለያየ መልክ ተቀምጠው ይገኛሉ። ለመጥቀስ ያክል በቀጥታ ወንጀሉን በሚደነግገው አንቀፅ ሥር /የወ/ሕ/አ 580 እና ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በተመለከተ በምዕራፍ ውስጥ በሚገኝ አንድ የሕግ ድንጋጌ ውስጥ /የወ/ሕ/አ 664/ የመሣሰሉትን ማስቀመጥ ይቻላል።

የተሻረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ የተበደለው ወገን ሲሞት በግል አቤቱታ የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮችን ማቅረብ እንደሚችል በግልፅ ተደንግጎ የነበረ ሲሆን ሕጉ ሲሻሻል ግን እነዚህ አጠቃላይ ድንጋጌዎች እንዲወጡ ተደርገዋል። በፍትህ ና ህግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት በተዘጋጀው ረቂቅ ላይ ግን ተካተው ይገኛሉ።

በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ጉዳዮች ተበዳዩ የወንጀሉን ድርጊት ወይም ወንጀል አድራጊውን ካወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ሦስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ለሕግ አስከባሪ አካላት መቅረብ አለበት። ያለ በቂ ሕጋዊ ምክንያት ከዘገየ አቤቱታውን መቀበል አይቻልም /የወ/ሕ/አ 213/። ፖሊስና ዐቃቤ ሕግ በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ጉዳዮች በወቅቱ ካልቀረቡ ምርመራም ጭምር መጀመር ስለሌለበት ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስም ሆነ የግል አቤቱታ ከቀረበለት ምርመራ እንዲጣራ ለሚመለከተው የፖሊስ አካል ማስተላለፍ አለበት። በአዋጅ ቁጥር 4/87 /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 23/4 መሠረት ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ወንጀል ተፈፅሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ የማዘዝ ሥልጣን ተሠጥቶታል። ፖሊስ ከየትም ወገን የቀረበን የወንጀል ክስ ተቀብሎ የማጣራት ኃላፊነት ስላለበት ከዐቃቤ ሕግ የቀረበም ቢሆን የተለየ አያደርገውም /የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 23/።

የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ የሚቀርበው በቃልም ሊሆን ይችላል። ዋናው ነገር ቃሉን የሚቀበለው ፖሊስ አቤቱታውን መዝግቦ በማንበብ አቤቱታ አቅራቢን ቀኑን ጭምር መዝግቦ ማስፈረሙ ላይ ነው (የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 14)። ሰውን በሀሰት የመወንጀል አሠራርን ለመከላከል ይህ አስፈላጊ ነው።

ጠkሚው ማንነቱን ሣይገልፅ የሚያቀርበው ክስ በጥንቃቄ ነው መታየት ያለበት። አንድ ሰው ማንነቱን ደብቆ ክስ የሚየቀርበው የግድ ሌላውን ለመጉዳት ብሎ ብቻ ላይሆን ይችላል። የበቀል ሥጋት ያደረበት ራሱን መደበቅ አማራጭ አድርጐ ሊወሰድ ይችላል። በአንድ በኩል ወንጀል ፈፃሚን እንዲጠየቅ የማድረግ የማነበረሰብ ጥቅም ያለ ሲሆን በሌላ በኩል ንፁህ ሰው ያለ ጥፋቱ ክስ ቀርቦበት ሰብዓዊ መብቱ እንዳይጣስ የማድረግ ተነፃፃሪ ጥቅም አለ። ሕጉ ሁለቱን ጥቅሞች ለማስታረቅ አማካይ የሆነ አማራጭን ነው የሚከተለው።

ጠቃሚው ማንነቱን ካላሣወቀ ምርመራ በፖሊስ የሚጠራው ጥቆማው ከፍ ያለ የሕግ መጣስን የሚመለከት ሆኖ በአካባቢያዊ ሁኔታዎች የተደገፈና የሚታመን መስሎ ከተገኘ ብቻ ነው(የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 12)። ይህም ሕጉ ኃላፊነቱን የሚወስድ ወገን ከሌለ ለዜጎች መብት ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚያደርግ ያረጋግጣል። ፖሊስ ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ በሚሰጥ መልኩ በመሥራት ጠቋሚውን ያልታወቀን ክስ በተመለከተ ምርመራ ከመጀመሩ በፊት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። ከፍ ያለ የሕግ ጥሰት ምን እንደሆነ በሕጉ ላይ በግልፅ አልተቀመጠም።

የወንጀል የፍትሕ ሂደት በወንጀል ክስ ወይም በግል አቤቱታ ሲጀመር ያለ አግባብ ክስ በንፁህ ዜጋ ላይ እንዳይቀርብ ሕጉ ያስቀመጠባቸውን አሠራሮች መከተል አስፈላጊ ነው። በሀሰት ሰውን የወነጀለ እንዲታወቅ ሊያደርግ በሚችል መልኩ የአቤቱታ አቅራቢን ማንነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ሆን ብሎ ሌላውን ለመጉዳት የሚቀርብ የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ በወ/ሕ/አ 447 መሠረት ያስጠይቃል። የተከሠሠ ሰው ነፃ በወጣ ጊዜ ሁሉ ክሱን ያቀረበ ወገን ራሱ በወንጀል ይጠየቃል ማለት አይደለም። መተኮር ያለበት ንፁህ የሆነን ሰው ወንጀል እንዳልፈፀመ እየታወቀ ሆነ ተብሎ የወንጀል ተግባር መኖሩን ማረጋገጡ ነው። ዜጎች ተበረታተው ወንጀልን ለመከታተል ዕገዛ እንዲያደርጉ እና በሌላ በኩል ያለ አግባብ ወንጀል ያልሠራ ሰው ክስ ቀርቦበት ሰብዓዊ መብቱ እንዳይገፈፍ አተገባበር ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

ስለዚህ የወንጀል ሕግ ሰት ሲኖር ጉዳዩ በፍትሕ አካላት ታይቶ ዕልባት እንዲያገኝ ሂደቱን ለማስጀመር ከሚያስፈልጉ ነገሮች ውስጥ አንዱ የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ መኖሩ ነው። ተገቢነት የሌላቸውን ክሶች ለመከላከል የሕጉን ዓላማ ተከትሎ የዜጎችን ሰብዓዊ መብት ለማስከበር መሥራት ያስፈልጋል። አውቆም ሆነ ሣያውቁ

ሕግን የመጣስ አሠራርን ለመከላከል ዐቃቤ ሕግ ከፖሊስ ጋር በቅርበት የመሥራት ኃላፊነት አለበት።

2.1.2. የእጅ ከፍንጅ ወንጀል አፈፃፀም

የፖሊስ ምርመራ ሥራ እንዲጀመር ሁልጊዜ የግድ አቤቱታ መቅረብ የለበትም። ወንጀሉ እጅ ከፍንጅ የሚባለለው ወንጀል አድራጊው ወንጀሉን ሲፈፅም ከተያዘ ወይም ለመፈፀም ሲሞክር ወይም ወንጀሉን እንደፈፀመ ወዲያውኑ ከተያዘ ነው (የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 19/1)። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ወንጀል መፈፀሙን ና ፈፃሚውን በቀላሉ መለየት ስለሚቻል ንፁህ ሰው ያለ አግባብ ሊወነጀልበት የሚችልበት አጋጣሚ ጠባብ ነው። የወንጀል ፍትሕ ሂደት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወዲያው መቀጠሉ የግድ አስፈላጊ ነው። በግል አቤቱታ ብቻ ለሚያስጠይቁ የወንጀል ተግባራት ግን ምንም እንኳን እጅ ከፍንጅ የተፈፀመ ቢሆንም ፖሊስ የተበዳዩን ይሁንታ ሣያገኝ ጉዳዩን ማስተናገድ መጀመር አይችልም። ተበዳዩ ፈቃዱን ከገለፀ ግን በተመጣጣይ ወዲያው ሂደቱ ይቀጥላል።

የእጅ ከፍንጅ ወንጀሎች የሚባሉት ከላይ የተጠቀሱት ብቻ አይደሉም። በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 19/2 እና 20 ሥር የተጠቀሱት ሌሎች መሠል ሁኔታዎችንም እንደ እጅ ከፍንጅ ወንጀሎች በሕጉ ይቆጠራሉ። እነዚህም ወንጀል አድራጊው የወንጀል ተግባሩን ከፈፀመ በኋላ ወዲያውኑ ሲሸሽ ምስክሮች ወይም ሕዝቡ የተከታተሉት ወይም የሕዝቡ ጩኸትና እሪታ የተሰማ እንደሆነ ወይም ወንጀል ተፈፀመ የተባለበት ቦታ ወዲያውኑ ፖሊስ የተጠራ እንደሆነ ወይም ወንጀሉ ሲፈፀም ወይም እንደተፈፀመ በቦታው የድረሱልኝ እሪታ የተሰማ እንደሆነ ነው። ወንጀለኛው ወዲያው አለመያዙ የእጅ ከፍንጅ ወንጀልነቱን አይቀይረውም። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች በቀላሉ ወንጀሉን ና የወንጀል ፈፃሚውን ማንነት መለየት ስለሚቻል የወንጀል ፍትሕ ሂደትን ያለሌላ ቅድመ ሁኔታ ሊቀጥል ይችላል። ንፁህ ሰው ሊወነጀልበት የሚችልበት አጋጣሚም ጠባብ ነው የሚሆነው።

በመሆኑም ወንጀሎች እጅ ከፍንጅ ከተፈፀሙ በግል አቤቱታ ብቻ የሚቀርቡ ወንጀሎች ከሆኑ የተበዳዩ አቤቱታ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ከተሟላ ሌላ ፎርማሊቲ ሣያስፈልግ በቀጥታ ያጠፋውን ወገን የሚጠይቅበት ሂደት ይጀመራል። ሰብዓዊ መብት መጠበቅ አለበት ማለት ወንጀለኛ መቀጣት የለበትም ማለት አይደለም። ወንጀል እንዲያውም በራሱ የሌላውን ሰብዓዊ መብት የሚጋፋ ማኅበራዊ ጠንቅ ነው።

የተበደለው ወገንም ሰብዓዊ መብት ጥበቃ ያስፈልገዋል። በእጅ ከፍንጅ ወንጀል ጊዜ በተጨባጭ ወንጀሎች ሲፈፀሙ በአፋጣኝ ያጠፋው ሰው ተይዞ በሕግ አግባብ እንዲጠየቅ መደረግ አለበት። የተፋጠነ ፍትሕ የማግኘት ሰብዓዊ መብቱም እግረ መንገዱን ይረጋገጥለታል።

በሌሎች ሀገሮችም የእጅ ከፍንጅ ወንጀሎች በተለየ ሁኔታ ነው የሚስተናገዱት። በእነግሊዝ next day justice በሚባል አሰራር በተፋጠነ ሁኔታ ጉዳዩ እልባት እነዲያገኝ ይደረጋል። በፈረንሳይ ሂደቱ real time dispatch ተብሎ ይታወቃል። በሀገራችንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ በስፋት እየተተገበረ ነው። ቀደም ብሎ ለቁልቢ ገብርኤል አመታዊ ሃይማኖታዊ ሥርአት የተወሰነ ነበር። አሁን ግን ጠቀሜታው በተጨባጭ ተረጋግጦ በመላ ሃገሪቱ በመተግበር ላይ ነው። በዚህ መሰረት እየተሰራ ወንጀል ተፈጸመ በተባለበት እለት ሁሉ በተፋጠነ ሁኔታ ለፍ/ቤት ጉዳዩ ቀርቦ እልባት እያገኘ ነው።

በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከጳጉሜ 5 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/2000 የተስተናገዱት የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ጉዳዮች አንደሚያረጋግጡት 91% የሚሆኑት ጉዳዮች እልባት ያገኙት በእለቱ ሲሆን 7% የሚሆኑት ደግሞ በማግሰቱ ውሳኔ አግኝተዋል። ሂደቱ በራሱ ተከሳሾች እነዲያመኑ ስለሚገፋፋ እና በዚሁ መልኩ እያመኑ አብዛኛው ጉዳይ ስለሚወሰን ለተፋጠነ ፍትህ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ በእጅ ከፍንጅ ወንጀል ጊዜ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በተፋጠነ ሁኔታ ሂደቱ ተጀምሮ መጠናቀቅ አለበት።

2.2. የወንጀል ፍትሕ ሂደት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

የወንጀል ሕግ ጥሰት ካለ ያጠፋ እንዲጠየቅ ሂደቱ ቀደም ብሎ በተገለፁት መንገዶች የሚጀምር ሲሆን፣ ሙሉ ሂደቱ በሕግ አግባብ ሣይጠናቀቅ ሊቋረጥባቸው የሚችልባቸው ሁኔታዎች አሉ። የወንጀል ሕጉ ሲሻሻል በግል ተበዳይ አቤቱታ የሚቀርቡ ጉዳዮች የሚቋረጡበትን ሁኔታ የሚገዙት ሥነ ሥርዓት ነክ ድንጋጌዎች የተሻሩ ቢሆንም የወንጀል ሕጉ ሥነ ሥርዓት ተሻሽሎ ሲወጣ ያካትታቸዋል ተብሎ ይጠበቃል። በረቂቁ ህግ ውስጥ ድነጋጌዎቹ ይገኛሉ። እከዚያም ቢሆን በወ/ሕ/አ 70/1 መሠረት አድራጊው የፈፀመው ወንጀል በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስቀጣና ተበዳዩ ወይም ሕጋዊ

ወኪሉ የፈቀደው ድርጊት ከሆነ አያስቀጣም። አንዴ ክስ ከቀረበ አሁን ባለው ሕግ ክስ በተበዳይ አቤቱታ የሚቀርብ ቢሆንም ማቋረጥ አይቻልም የሚለው ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር ነው የሚሆነው። ሕጉ በወንጀል አያስቀጣም ባለው ተግባር ሰው ሊቀጣ አይገባም። ሌላው ሊነሣ የሚገባው ነጥብ ተበዳይ የተባለው ሰው ክሱን አቅርቦ ከሞተ በኋላ ክሱ ሊቀጥል ይገባል ወይ? የሚለው ነው። ግለሰቡ ቢሞትም በእርግጥ ክሱ መቀጠል አለበት። ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በግል አቤቱታ የሚቀርበው የወንጀል ተግባሮች በሕጉ ይጎዳሉ ተብለው የሚገመቱት የተጐዳውን ወገን ነው። ይህ ከሆነ የሟቹ ወራሾች ቀርበው ክሱን አንፈልግም ብለው ካረጋገጡ ክሱ መቀጠሉ ጠቀሜታ አይኖረውም። መንግሥትና ሕዝብ በእንደዚህ ዓይነት ግላዊ ባህሪ ባላቸው የወንጀል ተግባራት ጋር የሚያገናኛቸው ነገር የለም። እራሱ ሕግ አውጪው ጉዳዮችን ለይቶ ግላዊ ናቸው ብሏቸዋል። ሟቹ በህይወት ስለሌለ ወራሾቹ ናቸው በሟቹ እግር ተተክተው ባለመብት መሆን ያለባቸው። ወራሾቹ ክሱን ካልፈለጉት መቀጠሉ አንዳችም ሕጋዊ ፋይዳ አይኖረውም። መቋረጥ አለበት።

በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ክሶች በየትኞቹ የፍትሕ አካላት ነው ጥያቄ በተጐጂው ሲቀርቡ ሊቋረጡ የሚችሉት? የሚለው በሕጋችን ላይ በግልፅ አልተቀመጠም። ጉዳዮቹ የግል ባህሪ ካላቸው ፖሊስ ምርመራ ማጣራት ከጀመረ በኋላ በተበዳዩ ክሱን እንደማይፈልግ ከተገለፀለት ይህንኑ አረጋግጦ መዝግቦ አስፈርሞ እራሱ ፖሊስ መዝገቡን መዝጋት ይችላል። የሚከለክለው ሕግ የለም የሚል ክርክር ይቀርባል። በሌላ በኩል ፖሊስ የሕግ ዕውቀቱ የዐቃቤ ሕግን ያክል ስላልሆነ ያለአግባብ ክሶችን በማቋረጥ ፍትሕ ለያዛባ ስለሚችል በምንም ዓይነት ሁኔታ ፖሊስ እራሱ ክስን የማቋረጥ ሥልጣን ሊሰጠው አይገባም። ሕግ አውጪው ይህንን ቢፈልግ በግልፅ ሥልጣኑን ይሰጠው ነበር የሚሉ ክርክሮች ይቀርባሉ። የተጠያቂነት አሠራር እንዲኖር መዝጋቱን ለዐቃቤ ሕግ በማሣወቅ ክሱን ራሱ ፖሊስ ቀሪ እንዲሆን ቢያደርግ ችግር ላይፈጥርም ይችላል። በረቂቁ ህግ አንቀጽ 54 መሰረት መርማሪ ፖ/ሊስ ለዐ/ህግ በማሳወቅ መዝገብ መዝጋት የሚችለው ለደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ብቻ ነው።

በግል አቤቱታ የሚቀርብ ክስ በተበደለው ወገን ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ጥያቄ እንዲቀርብ ከተደረገ በyላ ጉዳዩ ፍ/ቤት ደርሶ እንዲkረጥ ከተደረገ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 220/3 መሠረት ተበዳይ ለመንግሥት ወጪ መክፈል አለበት። ጉዳዩ ከዚያም በኋላም እንደ አዲስ ሊታይ አይችልም የመጨረሻ ይሆናል።

ሌላው ክስ ሊቋረጥ የሚችልበት መንገድ በዐቃቤ ሕግ ክሱ እንዲነሣ ሲደረግ ነው። በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ውስጥ የነበሩት ክሱን ዐቃቤ ሕግ እንዲያነሣ የሚፈቅዱ ድንጋጌዎች በሙሉ በአዋጅ ቁ. 39/85 ተሽረዋል። አሁን ዐ/ሕግ ክስን ለማንሣት ያለው የሕግ ድጋፍ አዋጅ ቁ. 4/87 /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 23/4 ነው። በዚህ አንቀፅ ዐቃቤ ሕግ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ማድረግ ወይም በሕግ መሠረት የወንጀል ክስ የማንሣት ሥልጣን ተሠጥቶታል።

በምርመራ ላይ ያለን የወንጀል ጉዳይ ለማስቆም ግልፅ ሥልጣን ለፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ተሠጥቶታል። የሚያነጋግረው አንድ ጊዜ ክስ ለፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ክስ ማንሣት ይችላል ወይ? የሚለው ነው። ሕጉ የሚለው በሕጉ መሠረት ክስ ያነሣል ነው። ክስ ለማንሣት በቀጥታ አይፈቀድም። በሕግ መሠረት ስለሚል ክስን ማንሣት የተመለከቱ ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች መፈለግ አለባቸው የሚሉ ክርክሮች ይቀርባሉ። በሌላ በኩል የዐቃቤ ሕግ ክስ የማንሣት መብት ሕጉ ሠጥቶታል። በቂ ምክንያት ክሱን ለማንሣት ካለ ሊቋረጥ ይችላል የሚሉ ክርክሮችም ይንፀባረቃሉ። ሕጉ ሲሻሻል ለእንደዚህ ዓይነቶች ችግሮች መፍትሄ መስጠት ይጠበቅበታል።

ለማጠቃለል በግል ተበዳይ አቤቱታ የሚቀርቡ የወንጀል ክሶች ተበዳይ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ወራሹን ጨምሮ ካልፈለጉዋቸው መቀጠላቸው ምንም ዓይነት ጠቀሜታ የላቸውም። ስለ ዐ/ህግ የወንጀል ሕጉ ሥነ ሥርዓት ሲሻሻል እንደዚህ ዓይነት መሰል ችግሮችን እንዲፈታ መደረግ አለበት።

የመወያያ ነጥቦች

1. የወንጀል ፍትሕ ሂደት እንዴት ይጀመራል? ንፁህ ሰው ያለወንጀሉ እንዳይጠየቅ ሕጉ ምን ዓይነት ጥበቃ ያደርጋል?

2. እጅ ከፍንጅ ወንጀልን በተመለከተ በሕጉ ላይ የተጠቀሰው «ወዲያው» የሚለው ቃል እንዴት መተርጉም አለበት?

3. በፖሊስ የመብት ጥሰቶች እንዳይፈፀም በሕገ መንግሥቱ እና በወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ ድንጋጌዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ ከዐቃቤ ሕግ ምን ይጠበቃል? ከፍ/ቤትስ?

4. በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 12 ሥር የተደነገገው ከፍ ያለ የሕግ መጣስ ተግባር እንዴት መተርጉም አለበት?

5. የወንጀል መፈፀምን ለፍትሕ አካላት ማሣወቅ ግዴታ ነው ወይ?

6. በግል ለሚቀርብ አቤቱታ በወ/ሕ/አ 212 መሠረት ወራሽ ክስ ማቅረብ ይችላል ወይ ?

7. በግል አቤቱታ ብቻ የሚቀርብ ክስ መታየቱ ከቀጠለ በኋላ የተበደለው ወገን ቢሞት ወራሹ ክሱ እንዲቋረጥ ማድረግ ይችላል ወይ?

8. ፖሊስ በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ክሶችን በተመለከተ ለተበደለው ወገን ጥያቄ ከቀረበለት በራሱ ክሱ ቀሪ እንዲሆን ማድረግ ይችላል ወይ?

9. በፌዴራልም ሆነ በክልል ባለው የሕግ ማዕቀፍ ዐቃቤ ሕግ ክስን ለማንሣት ሥልጣን አለው ወይ?

3. የፖሊስ ምርመራ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ሠልጣኞች በዚህ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ፡-

- ፖሊስ በፍ/ቤት ትዕዛዝ ተጠርጣሪን ሊይዝባቸው የሚችልባቸው ሕጋዊ ሁኔታዎች አውቀው በሥራ ላይ ያውላሉ::
- ፖሊስ ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተጠርጣሪን ሊይዝባቸው የሚችልባቸውን መንገዶች ይገልፃሉ፤
- በፍ/ቤት የመበርበሪያ ትዕዛዝ ሊመስጠን የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ተረድተው ይተገበራሉ፤
- ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ፖሊስ በብርበራ የወንጀል ፍሬዎችን ወይም ለወንጀል ማስረጃ የሚሆኑ ነገሮችን ለመያዝ ያለውን ሥልጣን ይዘረዝራሉ፤
- ከሕግ ውጪ የብርበራ ሥራ በፖሊስ መከናወን የሚያስከትለውን ውጤት ይተነትናሉ፤
- በተጠርጣሪ በወንጀል ማስረጃነት ደም መስጠትንና አሻራ ማንሣትን የመሣሰሉ ተግባራት በምን መልኩ በሕግ መሠረት ሊተገበሩ እንደሚችሉ ያስረዳሉ::

ፖሊስ በወንጀል መፈፀሙን ካወቀ ምርመራ በማከናወን ማጣራት አለበት:: በምርመራ ሂደት ስለሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ቀጥለን እንመለከታለን::

ወንጀል ስለመፈፀሙ መረጃ ከደረሰው ወይም ካወቀ ፖሊስ በተጨባጭ ማስረጃ ወንጀሉን ለማረጋገጥ ምርመራ ማከናወን አለበት:: የቀረበው ክስ ወይም መረጃ ቢያጠራጥረውም ምርመራ መደረግ ያለበት ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ጠቋሚው ላልታወቀ የወንጀል ክስ ነው:: ሰውን ለመጉዳት ሲባል ሊቀርብ ስለሚችል የዚህ ዓይነት ክስ ላይ የግድ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል:: ከዚህ ውጭ በምንም ምክንያት ፖሊስ ምርመራ ለማጣራት ወደ ኋላ ማለት አይችልም:: በሕግ አንድ ጊዜ የተጀመረን ምርመራ የማጣራት ሥራ ለማቋረጥ ለፖሊስ በሕግ በግልፅ የተሰጠው ሥልጣንም የለም:: በረቂቅ ሕጉ ላይ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን ዘግቶ ለዐቃቤ ሕግ ለማሣወቅ ሥልጣን ተሰጥቶታል:: በተበዳይ አቤቱታ የሚቀርቡ ጉዳዮችንም ጭምር እንዲያካትት ቢደረግ የዐቃቤ ሕግን ሥራ ሊያካትት ይችላል::

በፖሊስ ምርመራ ሂደት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ማስረጃ ማሰባሰብ እና ተጠ ርጣሪን መያዝ ናቸው። ከፖሊስ ምርመራ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ከወ/መ/ሕ/ቁ. 22 እስከ 37 እና ከወ/መ/ሕ/ቁ. 49 እስከ 62 የሚገኙት ናቸው። ከጊዜ ቀጠሮ ውጭ ግን የሚገኙት በዚህ ክፍል ይካተታሉ።

3.1. የማስረጃ አሰባሰብ

ተፈፀመ ስለተባለው ወንጀል ፖሊስ ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ መፈለግ አለበት። ወንጀል ጠቋሚ ወይም የተበደለ ወገን ወይም ከሌላ ከማናቸውም ሰው ማግኘት የሚገባውን መረጃ መሰብሰብ አለበት። በተለይ ስለ ጉዳዩ ከሚያውቁ ተበዳይ እና ምስክር ላይ ቃል መቀበል አለበት። የምስክር ቃል ሲቀበል ማረጋገጥ ያለበት የሙያ ምስክር ካልሆነ የምስክር የግል አስተያየታቸውን ሣይሆን ወንጀል መፈፀሙን ያወቁበትን መንገድ ነው። በስሜት ሕዋሶቻቸው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ያወቁተን እንዲገልፁ መደረግ አለበት። በደፈናው ወንጀል መፈፀሙን አውቃለሁ የሚል አገላለፅ ለተጠያቂነት አያመችም። በምን ዓይነት ሁኔታ እንዳወቀ ነው በምስክር መረጋገጥ ያለበት። ምስክሩ ስለጉዳዩ ያውቃል ወይም አያውቅም የሚለው ላይ አጣርቶ መወሰን የሚመለከተው የፍትሕ አካል ኃላፊነት ነው። በዐይኑ ከተመለከተ ወይም ከሰው ሰማ ወይስ በሌላ ተዘዋዋሪ መንገድ ከወንጀሉ ቦታ ሲሄድ አየ ወይስ በሌላ ዘዴ ስለጉዳዩ አወቀ። ለይቶ ካላስቀመጠ ያለአግባብ ሰዎች እንዲወነጀሉ በር ሊከፍት ይችላል። ይህንን ለመከላከል ፖሊስ በተጨባጭ ለቀጣዩ ምርመራ በሚረዳ እና ወንጀሉን ሊያረጋግጥ በሚችል መልኩ ቃል መቀበል አለበት።

ማንኛውም ሰው በፖሊስ ጥሪ ሲቀርብለት ቀርቦ የሚያውቀውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት። ፖሊስ ለምስክሮች ምንም ዓይነት የተሰፋ ቃል እንዲመሰክሩ መስጠት የለበትም። ምስክር ለመመስከር እየፈለገ ቃሉን ላለመቀበል ወደኋላ ማለት የለበትም።

በፖሊስ መሰባሰብ ያለበት ማስረጃ የሰው ብቻ አይለም። የቴክኒክ ማስረጃም መሰባሰብ አለበት። አሁን በሀገራችን ያሉት ከወንጀል ቦታ አሻራ ማሰባሰብን የመሳሰሉ ማስረጃዎችን መጠቀም ይገባል። የሠነድ ማስረጃዎችም ከተገኙ ማፈላለግ ተገቢ ነው። ወንጀሉን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ማናቸውም ማስረጃዎች በፖሊስ መሰብሰብ አለባቸው።

3.2. መያዝ/Arrest

ወንጀል ለመፈፀሙ መረጃ ካለው ፖሊስ ተጠርጣሪውን ማስቀረብ ይችላል። ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር የማዋል እንደነገሩ ሁኔታ በተለየ መንገድ ሊፈፀም ይችላል። ለተጠርጣሪው በፖሊስ መጥሪያ ተልኮለት ከቀረበ ፖሊስ በቁጥጥር ስር ያውላል። ከዚህ ውጪ መጥሪያ ተልኮለት ካልቀረበ ወይም ገና ያልተያዘ ከሆነ ፖሊስ ተጠርጣሪውን በሕግ ላይ በተደነገገው መሠረት በፍ/ቤት የመያዝ ትዕዛዝ ወይም ያለፍ/ቤት ትዕዛዝ ሊይዘው ይችላል። በየትኛውም መንገድ ተጠርጣሪው ይያዝ ፖሊስ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የተያዘን ሰው ሊለቅ ይችላል። ፖሊስ ተጠርጣሪውን በጣቢያ ዋስትና ሊለቅ የሚችልበት መንገድ በሕጉ ላይ ተለይቶ ተቀምጧል። ወንጀል ስለመፈፀሙ ቢጠራጠርም ቢያንስ በጣቢያ ዋስትና ነው ተጠርጣሪው መልቀቅ የሚችለው። በጣቢያ ዋስትና ለመልቀቅ ፖሊስ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.28 ስር የተመለከቱትን ጥብቅ ድንጋጌዎች መከተል አለበት። ከዚህ ውጪ ተጠርጣሪውን ፍ/ቤት በሕጉ ላይ በተመለከተው ጊዜ ማቅረብ ነው የሚጠበቅበት። ተጠርጣሪው መለቀቅ ካለበት አይቶ በዋስትና መልቀቅ የፍ/ቤት ኃላፊነት ይሆናል። ፖሊስ ያለሥልጣኑ ፈፅሞ ተጠርጣሪውን መልቀቅ የለበትም።

ተጠርጣሪው መያዝ ያለበት ሕግን በተመለከተ መንገድ ነው። ተጠርጣሪው በፖሊስ ተጠርቶ እራሱ ካልቀረበ ወይም ያለፖሊስ መጥሪያ መያዝ ያለበት ሆኖ ከተገኘ ፖሊስ ተጠርጣሪውን እንዲያዝ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ተጠርጣሪው በሁለት ዓይነት መንገድ ሊያዝ ይችላል። እነዚህም በፍ/ቤት ትዕዛዝና ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ናቸው። ያለፍ/ቤት ትዕዛዝ ለመያዝ ሕጉ በሚፈቅድበት ጊዜ ሁሉ ወደ ፍ/ቤት መሄድ ሣያስፈልግ በቀጥታ በራሱ ፖሊስ ተጠርጣሪውን መያዝ ይችላል። ሁለቱ የአያያዝ መንገዶች የየራሣቸው የተለየ ባህሪ ስላላቸው ለየብቻ እንመለከታቸዋለን።

3.2.1. በፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለ መያዝ

በመርህ ደረጃ ወንጀል ፈፀመ የተባለው ሰው መያዝ የሚችለው በፍ/ቤት ትዕዛዝ ብቻ ነው። የመያዣ ትዕዛዝ የፈለገ መርማሪ ፖሊስ በማናቸውም ቀንና ሰዓት ለፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። ሕጉ በመንግሥት የሥራ ሰዓት በማለት አልገደበውም። የተጠረጠረ ሰው ሊጠፋ የሚችልበት አጋጣሚ ስለሚኖር ከመደበኛ የሥራ ቀንና ሰዓት ውጪ ፍ/ቤቶች መሥራት አለባቸው።

የመያዣ ትዕዛዝ በፖሊስ በተጠየቀ ጊዜ ሁሉ በፍ/ቤት መፈቀድ የለበትም። በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 54 መሠረት የመያዣ ትዕዛዝ የሚሰጠው የተጠርጣሪው መቅረብ ፍፁም አስፈላጊ ከሆነ ብቻ ነው። ለዚህ ተግባር ፍ/ቤት ጅምር የፖሊስ ምርመራ መዝገብን ተመልክቶ በሕግ ወንጀል የተባለ ተግባር ተፈፅመ መባሉንና ወንጀል መፈፀሙን የሚያመለክት ማስረጃ ያስፈልጋል። ይህ ማለት ግን ፍ/ቤት ጥፋተኝነትን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ መኖሩን መመርመር አለበት ማለት አይደለም። በቂ ማስረጃ መኖሩ ወደፊት ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ በዐቃቤ ሕግ የሚመዘን ነው። ፍ/ቤቱ ማረጋገጥ ያለበት በበቂ ምክንያት ያቄው መቅረቡን ነው። ይህንን ለማረጋገጥ ወንጀል መፈፀሙን የሚያመለክት ማስረጃ በቂ ነው። (premafacia evidence)። እውነቱን ወዲያው ማረጋገጥ አይቻልም፤ ለምሣሌ አንድ ግለሰብ ወይም የፖሊስ አባል ተጠርጣሪው መጋዘን ውስጥ ሕገ ወጥ ዕቃ መኖሩን አረጋግጦ ቃል የሰጠበት ጉዳይ ቢሆን ተጠርጣሪው እንዲያዝ ለማስደረግ በቂ ነው። ፍ/ቤት ማስረጃ ምዘና ውስጥ መግባት የለበትም።

ተጠርጣሪን መያዝ ጊዜ የማይሰጥ ሊሆን ይችላል። ወንጀሉን ፈፅሞ ከአካባቢው ሊሰወር እንቅስቃሴ ላይ መሆኑን ለፖሊስ መረጃ ሊደርስ ይችላል። በዚህ ጊዜ ፖሊስ ለፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ እስከሚያቀርብ ድረስ ተጠርጣሪው ሊሰወር ይችላል። ሊፈጠሩ የሚችሉ ያልተጠበቁ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ሕጉ መፍትሄ አበጅቶለታል። በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 55 መሠረት አጣዳፊ ሁኔታ ሲያጋጥም መርማሪው ፖሊስ በቴሌፎን ወይም በቴሌግራም የመያዣ ትዕዛዝ መጠየቅ ይችላል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጥም የመያዣ ትዕዛዙ ከተፈቀደ በኋላ በ24 ሰዓታት ውስጥ በጽሑፍ ተደርጐ ለፍ/ቤቱ መቅረብ አለበት። ወሣኙ ነገር በተፈለገበት ጊዜ በአስቸኳይ ትዕዛዙ መገኘቱ ነው። ከዚያ በኋላ የተጠያቂነት አሠራር እንዲሰፍን ጥያቄው በጊዜ ተገድቦ መቅረቡ ተገቢ ነው።

3.2.2. ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለ መያዝ

ተጠርጣሪን ለመያዝ ሁልጊዜ ፍ/ቤትን የመያዣ ትዕዛዝ መጠየቅ አያስፈልግም። በሕጉ ላይ የተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ፖሊስ ፍ/ቤት ድረስ መሄድ ሣያስፈልገው በራሱ በቀጥታ ተጠርጣሪውን ይዞ በቁጥጥር ስር ማዋል ይችላል። ለፖሊስ ይህንን ሥልጣን የሚሰጡት ድንጋጌዎች ይዘት ሲታይ ያለ ፍ/ቤት

ትዕዛዝ መያዝ ልዩ ሁኔታም አይመስልም። በበርካታ ጉዳዮች ላይ ፖሊስ ያለ መያዣ ትዕዛዝ ተጠርጣሪን መያዝ ይችላል። እነዚህ ጉዳዮችን በመቀጠል እንመለከታለን።

ማንኛውም ሰው ወይም የፖሊስ ሠራዊት ከ3ወር በማያንስ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ የእጅ ከፈንጅ ወንጀል የፈፀመ እንደሆነ ተጠርጣሪውን መያዝ ይችላል። ፖሊስ ያልሆነ ሰው ተጠርጣሪውን ከያዘ በኋላ ወዲያው ለሚመለከተው የፖሊስ ክፍል ማስተላለፍ አለበት። የወንጀሉን ዓይነት ለመለየት መመልከት ያለብን የቅጣቱን መነሻ ሣይሆን መድረሻ ነው። መነሻው ቅጣት ዝቅተኛም ቢሆን መድረሻው ቅጣት 3 ወር ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ሕጉ ይሸፍነዋል።

ከዚህ ውጪ ለማንኛውም ሰው ሣይሆን ለፖሊስ ብቻ ተጠርጣሪን ያለፍርድ ቤት መያዣ ትዕዛዝ መያዝ የሚቻልባቸው ጉዳዮች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 51 ስር ተዘርዝረዋል። ከአንድ ዓመት በሚያንስ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ለመስራት ዝግጁ መነሻ ቅጣቱ አነስተኛም ቢሆን በዚህ ጊዜም ቤሆን መታየት ያለበት መድረሻው ቅጣት ነው።

የሕዝብን ፀጥታ በማበላሸት ላይ የሚገኝ ወይም የፖሊስን ስራ የሚያደናቅፍ ወይም ከታሰረበት የሚያመልጥ ወይም ለማምለጥ የሚሞክር ወይም ከፖሊስ ወይም ከመከላከያ ሠራዊት የከዳ ወይም በሕገ ወጥ መንገድ የቤት መሥሪያ ወይም ቤትን መስበሪያ መሣሪያ የያዘ ወይም የተሠረቀ ዕቃ መያዙ በሚገባ የሚጠረጠርን ወይም የወንጀል ፍሬ የያዘ ወይም በአደገኛ ቦዘኔነት በሚባ የተጠረጠረን ፖሊስ ፍ/ቤት መሄድ ሣያስፈልገው በቀጥታ በራሱ መያዝ ይችላል።

በመሆኑም ፖሊስ ፍ/ቤት መሄድ ሣያስፈልገው በብዙ ጉዳዮች ላይ ተጠርጣሪን በሕግ መሠረት መያዝ ስለሚችል የፍ/ቤትን ይሁንታ መጠየቅ የለበትም። ሕግን ተከትለ በራሱ መሥራት አለበት።

3.3. የዕምነት ቃል

በማናቸውም መንገድ በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋለ ተጠርጣሪ ማንነቱና አድራሻው ከተረጋገጠ በኋላ ለቀረበበት ክስ ወይም አቤቱታ ቃሉን መስጠት አለበት። ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ግን ለመናገር የማይገደድ መሆኑንና ፈቅዶ ግን የሚሰጠው ማናቸውን ቃል ተመዝግቦ በማስረጃነት ወደፊት ሊቀርብበት እንደሚችል ሊነገረው ይገባል። ይህ

ማይገለፅለት ቃሉን እንዲሰጥ ከተደረገ ውድቅ ሊደረግ ይገባል። ተጠርጣሪን ቃሉን እንዲሰጥ ማስገደድ ሕገ ወጥ ነው። በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘ የዕምነት ቃል ውጤቱ ምን እንደሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 19/5 ስር ተደንግጉ ይገኛል። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም።

በፖሊስ ጣቢያ የሚሰጥ ቃል ብዙ ጊዜ ፍ/ቤት ሲቀርብ ተቃውሞ ሲቀርብበት ይታያል። ተከሣሹ ተገድጄ ነው ካለ መገደዱን እራሱ ማረጋገጥ አለበት የሚል ክርክር ይቀርባል። በሌላ በኩል እራሱ ዓ/ህግ በተከሣሹ ከተካደ በነጻነት የተሰጠ ቃል ለመሆኑ በድጋፊ ማስረጃ ማስረዳት ይጠበቅበታል። ተከሣሹ ነጻነቱን አጥቶ ከእስር ላይ ስለሚገኝ በፈቃዱ ለመስጠቱ በከሣሽ ነው መረጋገጥ ያለበት በከሣሽ ከተረጋገጠ ነው ተከሣሹ መከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ያለበት የሚል ክርክርም ይቀርባል። በተጨማሪ ተከሣሹ የጣቢያ ቃሉ ውድቅ እንዲሆንለት ተገዶ ቃሉን ለመስጠቱ ማስረጃ ማቅረብ ያለበት ተከላከል ተብሎ ሣይነገረው ነው ወይስ ከተነገረው በኋላ መከላከያ ማስረጀ ሲያቀርብ አብሮ ያቀርባል በህጉ ላይ በግልፅ የተመለከተ ነገር የለም።

ተጠርጣሪው በፖሊስ ጣቢያ ቃሉን ሲሰጥ በፍቃዱ ለመስጠቱ ውዝግብ ስለሚፈጥር ተመራጩ መንገድ በወ/መ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 35 መሰረት ፍ/ቤት ሄዶ ቃሉን እንዲሰጥ ማድረግ ነው። ፍ/ቤቱ ቃሉን ከመቀበሉ በፊት በቅድሜያ በነጻነት መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት። ተጠርጣሪውን በመጠየቅ የሚሰጠው ቃል ወደ ፊት በማስረጃነት ሊቀርብት እንደሚችል ተገለጸለት ፈቃደኛ መሆኑን በማያሻማ መልኩ ማረጋገጥ አለበት። ይህ መደረጉም መዝገቡ ላይ መሰፈር አለበት። ተጠርጣሪው በነጻነት ቃሉን ከሰጠ በኋላ ተነቦለት ቃሉን የተሰጠበትን ቀን ጽፎ መፈረም ይጠበቅበታል። በመቀጠል ቃሉን የተቀበለው ዳኛ መፈረም አለበት። ከዚህ በኋለ ለዓ/ህግና ለሚመለከተው ሁሉ ቃሉ ተገልብጦ እንዲሰጥ ትእዛዝ ተሰጥቶ መዝገቡ መዘጋት አለበት። ምን ጊዜም አስተማማኝ የሆነውን በፍ/ቤት ቃል የማሰጠት አሰራር አላስፈላጊ ክርክርን ስለሚያስወግድ ፖሊስ ሊከተለው ይገባል። ነገር ግን ተከሳሹ በፍ/ቤትም ቢሆን በነጻነት ቃሉን ላለመስጠቱ መከላከያ ማስረጃ ካለው ማቅረብ ሊከለከል አይችልም።

3.4. መበርበርና መያዝ (Search and Seizure)

የፖሊስ ምርመራ አላማ ተፈፀመ የተባለን ወንጀል በማስረጃ ማረጋገጥ ነው፡፡ ለዚህ ተግባር ፖሊስ ማስረጃን ፈልጐ ማግኘት አለበት፡፡ ተርጣሪውን በሚያዝበት ጊዜ በሰውነቱ ማስረጃ ለወንጀሉ የሚሆን ማስረጃ ይዟል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ክሌለው በስተቀር አካሉን መፈተሽ የለበትም፡፡ በተግባር ግን ማንኛውም የሚያዝ ሰው ተፈተሾ ነው በቁጥጥር ስር የሚውለው፡፡ ይህ የሚደረገው ተጠርጣሪው ወደ ማረፊያ ቤት በራሱ ወይም በሌላው ላይ አደጋ ሊያደርስ የሚችል እቃ ይዞ እንዳይገባ ለመከላከል ይመስላል፡፡ ብርበራው መፈፀም ያለበት በተመሣሣይ ጾታ ነው፡፡ በብርበራ ማስረጃን ፈልጐ መያዝ የሚቻለው በህግ መሰረት በፍ/ቤት ትእዛዝ ና ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ ነው፡፡ ብርበራን የሚመለከቱት የወ/ወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 32 እና 33 ናቸው፡፡ ሁለቱንም በመቀጠል እንመለከታለን፡፡

3.4.1. በፍ/ቤት ትእዛዝ መበርበር ና መያዝ

በመሰረቱ ፖሊስ የብርበራም ተግባር በማከናወን ለማስረጃ የሚሆን ነገር መያዝ የሚችለው በፍ/ቤት ትእዛዝ ብቻ ነው፡፡ የብርበራ ትእዛዝ ለፍ/ቤት ጥያቄ ቀርቦ ሊገኝ ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱ ግን የመበርበሪያ ትእዛዙን በዘፈቀደ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ለፍትህ አላማ ወይም ለማናቸውም ፖሊስ ምርመራ ወይም ወንጀሉን ለማረጋገጥ የሚያስፈልግ መሆን አለበት፡፡ ፍ/ቤቱ ወንጀል ለመስራቱ በቂ ማስረጃ ካልቀረበ ለማለት አይችልም፡፡ መበርበሪያ ትእዛዝ የሚያሰፈልገው ራሱ ማስረጃ ለማፈላለግ ነው፡፡ ወንጀል መፈጸሙን የሚያመለክት ነገር ካለ በቂ ነው/prima fascia evidence/፡፡ ለምሣሌ የፖሊስ አባል ወይም ግለሰብ የስርቆት ወንጀል ፍሬ የሆነ እቃ ያለበትን ቦታ አረጋግጦ ከገለፀ በቂ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ብዙ ምስክር ለምን አልሆነም ወይም በቂ አይደለም የሚል ክርክር ሊቀርብ አይገባም፡፡ ፍ/ቤቱም ለፍትህ የቆመ አካል በመሆኑ ህግን ተከትሎ ፖሊስ ወንጀልን ለማረጋገጥ የሚያደርገውን እንቅሰቃሴ ማገዝ አለበት፡፡

የብርበራ ትእዛዝ አጠቃላይ ሊሆን አይችልም፡፡ በተናጠል የሚበረበረውን ና የሚያዘውን እቃ ለይቶ ማመልከት አለበት፡፡ ከመበርበሪያ ትእዛዝ ውጪ ፖሊስ ሌላ እቃ ለመያዝ አይችልም፡፡ ብርበራ በሚከናወንበት ጊዜ ገለልተኛ ታዛቢ ባለበት ቢሆን ተመራጭ ነው፡፡ የሚያዝ እቃ ዝርዝር በታዘቢ ፊት ተመዝግቦ በገለግለተኛ ሰው ሊፈረምበት ይገባል፡፡ የማያስፈልግ እቃ በደረሰኝ ተረጋግጦ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

ፖሊስ ብርበራውን ለማከናወን ከተፈቀደለት በኋላ ችግር ቢያጋጥመው ተመጣጣኝ ኃይል ሊጠቀም እና መበርበር ወዳለበት ቤት መግባት ቢከለከል ይህንኑ ሃይል ተጠቅሞ ለመግባት ይችላል፡፡ በፍ/ቤት በግልፅ ተለይቶ ካልተፈቀደለት በስተቀር ፖለስ ብርበራውን ከጠዋቱ 12፡00 እስከ ምሽቱ 12፡00 መድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ማከናወን አለበት፡፡

በመንግሥቱ አንቀፅ 26 መሰረት የግል ህይወት ጥበቃ ተደርጐለታል፡፡ መብቱ ግን ፍጹም አይደለም፡፡ በህግ በተመለከተ ልዩ ሁኔታ የሰው መኖሪያ ቤት፣ ሰውነትና ንብረት ሊበረበር ይችላል፡፡ ህግን በመተላለፍ ብራበራ ቢከናወን ውጤቱ ምን መሆን አለበት የሚለውን ህገ መንግስታችን በግልፅ አይሸፍነውም፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ግን በማያሻማ መልኩ እልባት ያገኘ ነው፡፡ በህገ ወጥ መንገድ እንዲገኝ ያስደረገውን በመቅጣት በህገ ወጥ ብርበራ የተገኘ ማስረጃ መቀበል አንድ አማራጭ ነው፡፡ ሌላ አማራጭ ህገወጥነት ላለማበረታታት ማስረጃውን ውድቅ ማድረግ ነው/the fruits of poisonous tree/፡፡ ህገወጥ ከተባለ ተቀባይነት ሊያጣ ይገባል/exclusionary rule/የሚል መከራከሪያ አለ፡፡ የትኛውን መከተል አለብን ያከራክራል፡፡ ህጋዊ የእስር ወይም የመበርበሪያ ትእዛዝ ይዞ ሣለ ፖሊስ ያላሰበውን የሌላ ወንጀል ማስረጃ ቢያገኝና ቢይዝስ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለውን በተመሣሣይ ያከራክራል፡፡ በህጋዊ ተግባር ላይ ከሆነ በብዙ ሀገራት ተቀባይነትን ያገኛል፡፡ ተቀባይነት(admissibility) ህግ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ግልጽ ከልካይ ህግ ያስፈልጋል፡፡ ከማስረጃ አግባብነት(relevance) ጋር ይለያል፡፡

አግባብነት ከሎጂክ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ማስረጃን ፍ/ቤት ሊቀበል አይገባም ስንል ሁልጊዜ የህግ ድንጋጌ ላይ መመስረት አለብን፡፡

3.4.2. ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ መበርበር ና መያዝ

ተጠርጣሪን እንደ መያዝ ሁሉ መበርበርና መያዝ ሁልጊዜ በፍ/ቤት ትእዛዝ ብቻ የሚፈፀም አይደለም፡፡ ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ ህግን ተከትሎ ብርበራ በማከናወን የወንጀል ማስረጃን መያዝ ይችላል፡፡ ያለ ፍ/ቤት የመበርበሪያ ትእዛዝ ብርበራ ማከናወን የሚቻለው ወንጀለኛውን እጅ ከፍንጅ ሲከታተሉ እና ቤት ውስጥ ገብቶ ከተደበቀ ወይም ወንጀል የተሰራበትን ነገር ቤት ውስጥ ያስቀመጠ ከሆነ ነው፡፡ ይህንን ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ፖሊስ የብርበራ ትእዛዝ ፍለጋ ወደ ፍ/ቤት ሲሄድ ወንጀለኛውን ወይም ማስረጃውን ላያገኝ ይችላል፡፡ ለዚህ ነው ህጉ በቀጥታ እርምጃ እንዲወሰድ የሚፈቅደው፡፡

ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ የፖሊስ ብርበራ የሚከናወንበት ሌላው መንገድ ከሶስት ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል ተፈፀመ ተብሎ ክስ ወይም አቤቱታ ከቀረበ በኋላ ለማስረጃ የሚሆን ወንጀሉ የተፈጸመበት ነገር የሆነ ቦታ ለመደበቁ ወይም ለመቀመጡ ለፖሊስ በሚያሣምን መልኩ ከተገለፀና የብርበራው ትእዛዝ እስኪገኝ ድረስ ማስረጃው ይጠፋል ተብሎ በበቂ ምክንያት የታመነ እንደሆነ ነው፡፡ የወንጀሉን አይነት ለመለየት መታየት የለበት መነሻው ቅጣት ሣይሆን መድረሻው ነው፡፡

በመንገድ ላይ ወይም ወደ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ለመግባት የሚደረግ ፍተሻ ህጋዊነት ላይ ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡፡ በመንገድ ላይ የሚደረገው ፍተሻ /stop amd frisk/ በሚፈተሸው ሰው ፈቃድ ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ ሊያወዛግብ ይችላል፡፡ ወደ ተቋም የሚገባ ሰው ግን ያልፈለገ ሊመለስበት የሚችል ሁኔታ ስላለ ከግል ነጻነት መጣስ ጋር ያለው ግንኙነት አነስተኛ ነው፡፡ መታየት የለበት ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የግል ነጻነት መከበሩን የመጠየቅ ሁኔታ/reasonable expectation/ ላይ ነው፡፡ ህገወጥነት ካለ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለው ቀደም ብሎ የተገለጸው እዚህ ጋርም አግባብነት ይኖረዋል፡፡ ሰለሆነም

የወንጀል ህግ ሥነስርዓቱ ሲሻሻል ያሉት ክፍተቶችን ሁሉ በሚዘጋ መልኩ ሊቀረፅ ይገባል፡፡ ባለውም ህግ ቢሆን ህገ መንግስቱን ተከትሉ መስራት ይገባል፡፡

3.5. ከተጠርጣሪ አካል ላይ የሚወሰድ ማስረጃ

ወንጀል ተፈጸመ ተብሎ ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ማስረጃ የሚሆን ነገር ከሰውነቱ ላይ ለማግኘት ፍቃደኛ ካልሆነ ምን መደረግ አለበት የሚለው በህጋችን ግልፅ ምላሽ አላገኘም፡፡ በዚህ ጊዜ ሁለት አማራጭ ነው ያሉት፡፡ አንዱ ተጠርጣሪውን በሃይል በማስገደድ የጣት አሻራ ወይም የደም ምርመራ እንዲደረግ ነው፡፡ ሌላው አማራጭ በምርመራ የሚገኘው ውጤት ተጠርጣሪው ተመርምሮ ውጤቱ በአግባቡ እንዲረጋገጥ ካልፈለገ ባይመረምር የራሱ ችግር በመሆኑ ኖረበትም አልኖረበትም እንዳለበት ቆጥሮ ማለፍ ነው፡፡

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 34/1 መሰረት በፍ/ብ/ህ/ቁ 20 ሥር የተደነገገው ቢኖርም መረማሪው ፖሊስ ተከሣሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ተመልክቶ በህኪም መመርመር የሚያስፈልገው መሆኑን ከተረዳ የማከም ፍቃድ ያለው ሐኪም ምርመራውን እንዲያደርግ ና የምርመራውን ውጤት ሐኪሙ በፅሑፍም እንዲያስታውቀው ለማዘዝ ይቻላል፡፡ ስልጣኑ የተሰጠው ለፖሊስ ነው፡፡ ይህ ግልፅ ድንጋጌ ነው፡፡ ሊገደድ ይገባል፡፡ ተመርማሪው ባይፈልግም ለወንጀል ጉዳይ ሊገደድ ይገባል ለፍታብሄር ግን እንዳለበት ግምት ነው መወሰ ያለበት በማለት መከራከር ይቻላል፡፡

በፍ/ብ/ህ/ቁ 20 መሰረት የዚህን አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም መደረግ ያለበት በምርመራ ሊገኝ የሚችለው ነገር እንዳለበት በመገመት ውሣኔ መስጠት ነው፡፡ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 34/1 የፍታብሔር ህጉ ድንጋጌ ቢኖርም ተብሎ ስለተቀረፀ ተጻሚነት አለው፡፡ ተጠርጣሪው ተገዶ መመርመር አለበት ወይም ተመጣጣይ ለህዝብ ጥቅም ሲባል አሻራ መስጠት አለበት ሊባል ይችላል፡፡

በኤች አይ ቪ ፖሊሲው ላይ ግን ማስገደድ ተከልክሎዋል፡፡ በህግ አተረ[1]ጎም ፖሊሲ ከህግ በላይ ሊሆን አይችልም፡፡ ቢሆንም ቅለ አፈጻጸም ላይ የራሱ

አንደምታ አለው፡፡ በአሰሪ ና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14/2/መ ስርም ለኤች አይ ቪ ምርመራ ሰራተኛን ማስገደድ አይቻልም፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀፅ 19/5 መሰረት ደግሞ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፡፡ በአንቀፅ 26 ስርም የግል ነጻነት ተከብሯል፡፡ ከዚህ አንጻር የማስገደድን ተግባርን ህገ መንግስታዊነት መመልከት ያስፈልጋል፡፡ እንዳለበት ገምቶ ማለፍ ይሻላል ከተባለ ግን ፖሊስ በጥንቃቄ በታዛቢ ወይም በፍ/ቤት የተጠርጣሪውን እምቢተኝነት አረጋግጦ መያዝ አለበት፡፡ ሴትን ደፍሮ ወዲያው አልመረመርም ብሎ በግብረ ስጋ ግንኙነት ሊተላለፍ /Sexually transmitted diseases/ ጨብጥን ለመሣሰሉ በሽታዎች መድሃኒት ከወሰደ በኋላ ዘግይቶ ልመርመር የሚል ጥያቄ እንዲያቀረብ በር መክፈት የለበትም፡፡

በአሜሪካ ፌዴራል ና በብዙ ክልሎች እነዲሁም በአንዳንድ አውሮፓ ሀገራት ራስን በወንጀል ያለ መገደድ መብት/the privilege against self-incrimination/ ሃሳብን ከመግለፅ ጋር ብቻ ነው የሚያያይዙት፡፡ ተገዶና የጣት አሻራ ከመስጠት ጋር እንዲሁም ፎቶግራፍ ከመነሣትና ከመለካት ጋር አይገናኝም ተብሎ ነው የተወሰደው፡፡ በረቂቁ የሃገራችን የወንጀል ሥነ ስርዓት ህግ ላይም በፍ/ቤት ፍቃድ ምርመራ ማከናወን ተፈቅዷል፡፡

በአሜሪካ ስላለው ሁኔታ Jerold H. Israel እና Wayne R. Lafave በተባሉ ፀሃፍት መፅሐፍ ውስጥ የሰፈረውን እዚህ ጋር ማስቀመጡ ጉዳዩን ለማብራራት ስለሚረዳ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡-

> *In schmerber v. cal./1966/, the court upheld the taking of a blood sample by physician at police direction from defendant over his objection after his arrest for drunken driving... The court...rejected this contention and held that the privilege protects an accused only from being compelled to testify against himself, or other wise provide the state with, evidence*

of a testimonial or communicative nature...the privilege only protects one from being compelled to express the contents of his mind...

በዚህ ፅሑፍ ላይ በተጨማሪ ይኸው አላማ የተገለፀውን አባባል የሚያጠናክር ነገር ሰፍሮ የሚገኝ ሲሆን እሱንም ማስቀመጡ ሁኔታውን ለመገንዘብ ስለሚጠቅም እንዳለ ማስፈሩ ተመርጧል፡-

... both federal and state courts have usually held that it offers no protection against compulsion to submit to finger printing, photographing or measurements,...

በሃገራችንም ቢሆን ህገመንግሥቱ ለመከላከል የፈለገው የሚመስለው በፖሊስ ድብደባ በሰው ልጅ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጭካኔ የተሞላበት ድብደባ ና ማሰቃየት ነው፡፡ ደም ና የጣት አሻራን መስጠት የመሳሰሉት ጉዳዩችን ማካተት የለበትም፡፡ ነገር ግን ይህ አከራካሪ በመሆኑ የመንግስትን ግልፅ የፖሊሲ ና የህግ ውሳኔ የሚሻ ነጥብ ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ክፍል የተነሱ የህጉን ችግሮች በሚያስወግድ መልኩ የወንጀል ህግ ሥነ ስርዓት ፀድቆ ስራ ላይ መዋል አለበት፡፡ባለውም ህግ ቢሆን የህገ መንግስቱን አላማና መንፈስ ተከትሎ ህጉን በመተርጐም ሥራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡

የመወያያ ነጥቦች

1. ተከሣሽ ለፖሊስ የሰጠውን ቃል በነፃነት አልሠጠሁም ቢል የማስረዳት ሸክሙ በቀጥታ ተከሣሹ ላይ ይወድቃል ወይስ ዐቃቤ ሕግ በቅድሚያ በነፃነት ቃሉ መሰጠ ቱ በደጋፊ ማስረጃ የደረጃ ምስክርን በመሳሰለ ማረጋገጥ አለበት?

2. ለፍ/ቤት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 35 መሠረት የተሰጠ ቃል በማስረጃነት ሲቀርብ ተቃውሞና መከላከያ ሊቀርብበት ይችላል ወይ?

3. በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 25 መሰረት ፖሊስ ምርመራ አጣርቶ ተጠርጣሪው ወንጀል መፈፀሙን የሚያሣይ ማስረጃ ቢያጣ ተጠርጣሪውን ማስቀረብ ነው ያለበት ወይስ መዝገቡን ለዐቃቤ ሕግ ማስተላለፍ?

4. በተጠርጣሪው ላይ በፍ/ቤት የመያዝ ትዕዛዝ የሚሰጠው ምን ዓይነት ሁኔታዎች ሲረጋገጡ ነው?

5. ያለፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ፖሊስ ተጠርጣሪን የሚይዝባቸው ሁኔታዎች ምንድናቸው?

6. ፖሊስ ተጠርጣሪውን በጣቢያ ዋስትና የሚለቅባቸው ሕጋዊ መንገዶች ምንድናቸው?

7. በፍ/ቤት የመበርበሪያ ትዕዛዝ ለመስጠት ምን መረጋገጥ አለበት?

8. ያለ ፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ብርበራ በፖሊስ ሊካሄድባቸው የሚችልባቸው ሁኔታዎች ምንድናቸው?

9. ለምሳሌ በአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተጠረጠረ ሰው ለኤችአይቪ ወይም በግበረ ሥጋ ግንኙነት ለሚተላለፍ በሽታ እንዲመረመር ተጠይቆ ፍቃደኛ ባይሆን ሊገደድ ይገባል ወይ?

10. በወንጀል የተጠረጠረ ሰው አሻራ ለመስጠት ፍቃደኛ ባይሆን ሪኮርድ እንዳለበት ለማጣራት በኃይል እንዲሰጥ ሊደረግ ይገባል ወይ?

11. በሕጋዊ እስር ለማጣራት ወይም ብርበራ አጋጣሚ ያልታሰበ የወንጀል የሌላ ማስረጃ ቢገኝ ውጤቱ ምን ይሆናል?

12. **በማስገደድ ወይም በሕገ ወጥ ብርበራ የተገኘ ማስረጃ ቢቀርብ ሕጋዋ ውጤቱ ምን መሆን አለት? በህገ ወጥ መንገድ በብርበራ ስለተገኘ ማስረጃ ውጤት በህገ መንግስቱ በግልጽ የተደነገገ ነገር አለመኖሩን እንዴት ያዩታል?**

13. **መንገድ ላይ ወይም ወደተለያዩ መንግሥታዊ የሆኑ ወይም ያልሆኑ ተቋማት ለመግባት የሚደረግ ፍተሻ ሕገ ወጥ ነው ወይ?**

4. የጊዜ ቀጠሮ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህንን ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች፡-

- **የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በወንጀል የተጠረጠረን ሰው ሰብአዊ መብት ለማረጋገጥ ያለውን ሚና ተገንዝበው ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡**
- **በወንጀል የተጠረጠረ ሰው የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ከቀረበ በኋላ የሚፈጸሙ ስነ ስርዓቶችን አውቀው በሥራ ላይ ያውላሉ፡፡**

በወንጀል ተጠረጠረ ሰው በፖሊስ ከተያዘ በኋለ ፍ/ቤት መቅረብ ያለበት ሲሆን የዚህን አሰራር ጠቀሜታና ተጠርተው ፍ/ቤት ከቀረበ በኋላ የሚፈጸሙ ስነስርዓቶችን እንመለከታለን፡፡

ፖሊስ ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ዜጉችን ያለአግባብ በመያዝ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተግባር እንዳይፈጽሙ ለመከላከል ሐገራት በህግ ከሚያደርጉት ጥበቃ አንዱ በህገ መንግስት መሰረት የተያዘ ሰው ፍ/ቤት በህግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲቀርቡ ማድረግ ነው፡፡ በሀገራችንም ይህ መብት በ ህገ መንግሥስቱ አንቀፅ 19/3 እና በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 29/1 መሰረት በወንጀል ተጠርጥረው ለተያዙ ሰዎች የተረጋገጠ መብት ነው፡፡

ተጠርጣሪው ከተያዘ በኋላ ፍ/ቤት ወዲያውኑ እንዲቀርብ የሚያስፈልገው የእስሩን ህጋዊነት ለማረጋገጥ ነው፡፡ ተጠርጣሪው እንደቀረበ ፍ/ቤቱ ማንነቱን አረጋግጦ ከመዘገበ በኋላ በምን ዓይነት ወንጀል ተጠርጥሮ እንደተያዘ ለተጠርጣሪው ሊገለፅለት ይገባል፡፡ ከዚህ በኋላ ፖሊስ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን ፍ/ቤቱ አረጋግጦ ተጨማሪ ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ ምክንያቱን ከፖሊስ ማጣራት አለበት፡፡ የተጠርጣሪውም ሐሳብ መሰማት አለበት፡፡ ተጨማሪ ጊዜ የሚፈቀድበት በቂ ምክንያት ከሌለ እና የተጠረጠረበት ወንጀል ዋስትና የማያስነፍግ ከሆነ ተጠርጣሪው በዋስትና እንዲለቀቅ ፍ/ቤቱ ማዘዝ አለበት፡፡ የጊዜ

ቀጠሮ ችሎቱ ፖሊስ ያቀረበው ተጨማሪ ምርመራ የማጣሪያ ጊዜ ላይ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት የተጀመረ የፖሊስ ምርመራ የደረሰበትን ደረጃ ለማወቅ፣ የቀረውን ምርመራ ለማጠናቀቅ፣ ተጠርጣሪው በእሰር ላይ መቆየት አስፈላጊነት እና የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ጊዜ ለማረጋገጥ ፖሊሱን በመጠየቅ እና እንደአሰፈላጊነቱ የፖሊስ ምርመራ መዝገብን በመመልከት ማጣራት ይጠበቅበታል፡፡

የተጠርጣሪው የመደመጥ መብትን ምንጊዜም ቢሆን መዘንጋት የለበትም፡፡ በተግባር ጥያቄ የሚያስነሣው የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ስልጣን ወሰን ነው፡፡ ችሎቱ ተጠርጣሪው ያለ አግባብ የተያዘ መሆኑን ቢያረጋግጥ ያለ ዋስትና ሊለቅው ይችላል ወይ? የሚለው ያከራክራል፡፡ በህጉ ላይ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ከመፍቀድ እና በዋስትና ከማሰናበት ውጪ የተቀመጠ ሌላ 3ኛ አማራጭ የለም፡፡ ከዚህ አንጻር ችሎቱ ተጠርጣሪውን በዋስትና ብቻ ነው መልቀቅ ያለበት ሊባል የችላል፡፡ ነገር ግን በስህተት መያዙን ፖሊስ ጭምር እያረጋገጠ ዋሰትና አቅርብ ማለት ትርጉም ለውም፡፡ ዋስትና እራሱን በቻለ የተለየ ክፍል በቀጣይነት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

ከጊዜ ቀጠሮ ችሎት ሥልጣን ጋር በተያያዘ ሌላ ሊነሣ የሚገባው ነጥብ ፖሊስ ምርመራውን ያለበቂ ምክንያት ባያጠናቅቅ ወይም ዓ/ህግ የምርመራ መዝገቡ ደርሶት በወቅቱ ውሣኔ ሣይሰጥበት ቢቀር እና ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን የወንጀል ጉዳይ ዋስትና የሚያስነፍግ ቢሆን የሚፈጠር ሁኔታ ነው፡፡ የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ ተጠርጣሪው እንዲለቀቅ ወይም በእስር እንዲቆይ ትእዛዝ ሣይሰጥ የመዝጋት አሰራሩን የሚከተሉ ዳኞች ያጋጥማሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ፖሊስ ተጠርጣሪውን የመልቀቅ ወይም ያለመልቀቅ ችግር ውስጥ ይገባል፡፡ ተጠርጣሪው ህግን የሚያውቅ ወይም ጠበቃ ካለው ያለው አማራጭ አካልን ነጻ የማውጣት ክስ /habeas corpus/ለፍ/ብሔር ችሎት ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አሰራር ሊገመት ለማይችል ሁኔታ ተጠርጣሪውን የሚያጋልጥ ነው፡፡ ተጠርጣሪው ለረጅም ጊዜ በእሥር ላይ ሆኖ ሊንገላታ የሚችልበትን በር ይከፍታል፡፡ ከዚህ የተሻለው አማራጭ ለሚመለከተው ዓ/ህግ ኃላፊ ፍ/ቤቱ በትእዛዝ ለማሣወቅ ወይም በማስጠራት መፍትሔ እንዲገኝ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም መንገድ ውጤት ካልተገኘ

እስከ መጨረሻ ዓ/ህግ ኃላፊ ድረስ ሁኔታው እንዲታወቅ በማድረግ ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ መደረግ አለበት፡፡ በሂደት ውስጥ የሥራ ግዴታውን የጣሰ ካለ ለሚመለከተው አካል በማሣወቅ ተጠያቂነት እንዲኖር ማስደረግ ይቻላል፡፡ ፍ/ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበት እንደነገሩ ሁኔታ ትእዛዝ መስጠት አለበት እንጂ የዜጎችን ሰብዓዊ መብት አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ ጉዳዩን አንጠልጥሎ መተው የህግ የበላይነትን ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ የሚያደርግ ነው የሚሆነው፡፡

ፍ/ቤት ምን ያህል ጊዜ የጊዜ ቀጠሮ ሊፈቅድ እንደሚችልም በህጉ ላይ በግልጽ ያልተመለከተ ቢሆንም ያለበቂ ምክንያት ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድ አይገባም፡፡ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዳይኖር የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በጥቅቃቄ እያንዳንዱን ጉዳይ እያጣራ መፍቀድ አለበት፡፡ በአግባቡ ይህ ከተተገበረ የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ አያስፈልግም፡፡ የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ ጠቀሚታ ቢኖረውም የራሱ የሆነ ችግር ሊያስከትል ይችላል፡፡ ለምሳሌ ተጠርጣሪው ከህግ ውጪ ከሌሎች የወንጀል ተሳታፊዎች ጋር በመሆን ሴትን ጠልፎ የደበቀ ቢሆን እና የተጠለፈችው እንዳትለቀቅ የተያዘው ተጠርጣሪ ለመተባበር ባይፈልግ ወይም የተለዩ የተወሳሰቡ ጉይዮች ቢየጋጥሙ እና ምርመራው በህግ የተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ ባይቻል ሊፈጠር የሚችለውን አስቸጋሪ ሁኔታ አስቀድሞ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ 14 ቀን ተጨማሪ ምርመራ የማጣሪያ ጊዜ የእረፍት ና የበዓል ቀናትን ያካትታል ወይ? የሚል ጥያቄ በተጨማሪነት ከጊዜ ቀጠሮ አፈቃቀድ ጋር ተያያዞ ይነሣል፡፡ የዋስትና ጉዳይ እራሱን ችሎ በቀጣይነት የሚታይ ቢሆንም ከጊዜ ቀጠሮ ችሎት ጋር ተያይዞ ሣይነሣ መታለፍ የሌለበት አንድ ነጥብ አለ፡፡ ዋስትና በጊዜ ቀጠሮ እና በመደበኛ ሁኔታ ክስ በዓ/ህግ ከቀረበ በኋላ ታይቶ የሚፈቀድበት አሰራር አለ ፡፡ ተጠርጣሪው ከመደበኛ ክስ ከተመሰረተበት በኋላ ባይቀርብ የጊዜ ቀጠሮ በተገባው ዋስትና መሰረት ተከሣሹን እንዴት ማስቀረብ እንደሚቻል በህጉ ላይ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ ተከሣሹ ከጠፋበት በጊዜ ቀጠሮ ላይ ዋስትናው የሰው ቢሆንና ዋሱ ሊያቀርበው ባይችል የዋስትናው ገንዘብ ገቢ እንደሆን መታዘዝ ያለበት በጊዜ ቀጠሮው መዝገብ ላይ ነው

ወይስ በመደበኛው መዝገብ ላይ፤ ማነው ጥያቄውን አቅርቦ ማስወሰን ያለበት ዓ/ህግ ወይስ ፖ/ሊስ ህጉ ምላሽ የለውም፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች መቅረፍ የተዘጋጀው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ ረቂቅ አሁን ካለው ህግ መሰረታዊ ልዩነት የሌለውና የህጉን ችግሮች የማይቀረፍ በመሆኑ ይበልጥ ትኩረት ተሰጥቶ ተሻሽሎ ሊያሰራ በሚችል መልኩ መፅደቅ አለበት፡፡ በረቂቁ ላይ ለጊዜ ቀጠሮ የጊዜ ገደብ 6 ወር ተብሎ የተቀመጠ ሲሆን ይህ ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች ችግር ሊፈጥር ስለሚችል ሊታሰብበት ይገባል፡፡ የጊዜ ገደቡ ባይከበርስ ምን ውጤት ይኖረዋል የሚለው ምላሽ ያገኘ ባለመሆኑም እንደገና ሊፈተሽ ይገባል፡፡ በመሆኑም አሁን የለው ህግ ና ረቂቅ ህግ ያለባቸው ችግሮች በሚገባ ተጠንቶ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ፀድቆ በስራ ላይ መዋል አለበት፡፡

የመወያያ ነጥቦች

1. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በፖ/ሊስ በወንጀል ተጠርጥሮ የተየዘ ሰው እንደቀረበ ለተጨማሪ ጊዜ ተጠርጣሪው በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ከማዘዙ በፊት ወይም በዋስትና እንዲለቀቅ ከማድረጉ በፊት ምን ማድረግ አለበት?

2. በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 59/3 መሰረት የሚሰጠው ተጨማሪ የፖ/ሊስ ምርመራ ማጣሪያ የ14 ቀን ጊዜ ከመንግሥት የስራ ቀናት ውጪ የሆኑትን የእረፍት ቀናትና የበአላት ቀን ያካታታል ወይ?

3. ዋስትና በህግ በሚያስነፍግ ጉዳይ ላይ ፖ/ሊስ ያለ በቂ ምክንያት ምርመራውን ሳያጠናቅቅ ወይም ምርመራው ተጠናቆ የምርመራ መዝገቡ ለዐ/ህግ ከተላከ በኋላ በአፋጣኝ ውሣኔ ሣይሰጥበት ቢቀር የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ምን ማድረግ አለበት?

4. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ዋስትና የሚያስነፍግ የወንጀል ጉዳይ የተጠረጠረን ግለሰብ ያለ አግባብ መያዙን ቢያረጋግጥ ሊለቀው ይችላል ወይ?

5. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ፖሊስ ያለ በቂ ምክንያት ለተጨማሪ ጊዜ ተጠርጣሪውን በእስር ለማቆየት ጥያቄ በማቅረቡ ምክንያት መዝገቡን ተጠርጣሪው እንዲለቀቅ ሳያዝ ወይም ዋስትና ሳይፈቅድ ቢዘጋው በተጠርጣሪው መብት ላይ ምን ዓይነት ተፅእኖ ያሣድራል? የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ተጠርጣሪው በምን መልኩ ህጋዊ መብቱን ማስከበር ይችላል?

6. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በወንጀል ተጠርጥሮ የተየዘ ሰውን ያለአግባብ መያዙን ቢያረጋግጥ ያለዋስትና ሊለቅቀው ይችላል ወይ?

7. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ተጨማሪ የምርመራ ማጣሪያ የሚፈቅድበትን ጊዜ በህግ ገድቦ መስቀመጥ ምን አይነት ጥቅምና ጉዳት ይኖረዋል፡፡

8. በጊዜ ቀጠሮ ችሎት አንድ ጊዜ ዋስትና ከተገባ በኋላ ምርመራው ተጠናቆ በዓ/ህግ ለፍ/ቤቱ የወንጀል ክስ ሲቀርብለት ሌላ አዲስ የዋስትና ተከሣሹ እንዲያቀርብ ማደረግ ተቀባይነት ያለው አሰራር ነው ወይ?

9. ለዓ/ህግ የወንጀል ክስ ከተመሰረተ በኋላ የተከሰሰ ሰው በጊዜ ቀጠሮ ችሎት ዋስትና ግዴታ ከገባ በኋላ ቢሰወር መደበኛ ችሎቱ በጊዜ ቀጠሮ ዋስትና ግዴታ ላይ ትእዛዝ ማስተላለፍ ይችላል ወይ ?

5. ቀዳሚ ምርመራ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ሠልጣኞች ይህንን ክፍለ ትምህርት እንዳጠናቀቁ፦

- **ቀዳሚ ምርመራ ምን እንደሆነ ያስረዳሉ፤**
- **ቀዳሚ ምርመራ ማድረግ ምን ጠቀሜታ እንዳለው ተረድተው ለተግባራዊነቱ በፅናት ይቆማሉ፤**
- **ቀዳሚ ምርመራ በማድረግ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራትን ለይተው አውቀው በተግባር ላይ ያውላሉ።**

በዚህ ክፍል ቀዳሚ ምርመራ ምን እንደሆነ ይብራራል። ቀዳሚ ምርመራ ማድረግ ምን ጠቀሜታ እንዳለውም ይካተታል። በተጨማሪም ቀዳሚ ምርመራ በማድረግ ሂደት ውስጥ መፈፀም ያለባቸው ዋና ዋና ተግባራት ምን እንደሆኑም ተለይተው ይቀመጣሉ።

ቀዳሚ ምርመራ በተለይ የኮመን ሎው የህግ ስረአትን በሚከተሉ ሀገራት ሚከናወነው ተጠርጣሪው በወንጀል እንዲከሰስ ለማድረግ በቂ ማስረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ ነው። በቂ ማሰረጃ ከሌለ በፍ/ቤት በነጻ መሰናበት አለበት። በሌሎች ሀገሮች ሂደቱ የሚያስፈልገው ማስረጃን ጠብቆ ለማቆየት ነው። በሃገራችንም የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ቀዳሚ ምርመራ የሚከናወነው በከባድ የወንጀል ጉዳዮች የፖሊስ ምርመራ ተጠናቆ በዐቃቤ ሕግ ክስ በሚመሠረትበት ጊዜ ምሥክሮች አድራሻ በመቀየር ወይም ሞትን በመሳሰለ ምክንያት ላይገኙና ላይመሠክሩ የሚችሉበትን ሁኔታ ለመከላከል ማስረጃን ጠብቆ ለማቆየት የሚፈፀም የጥንቃቄ ሥርዓት ነው። ማስረጃ ሰምቶ ተከሣሹን በነፃ የማሠናበት አንዳችም ውጤት አይኖረውም። ቀዳሚ ምርመራን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 85 እስከ 93 የሚገኙት ናቸው።

ቀዳሚ ምርመራ የሚደረግባቸው የወንጀል ጉዳዮች በሁለት መደብ ይከፈላሉ። የመጀመሪያዎቹ በግዴታ ሁልጊዜ ቀዳሚ ምርመራ ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህም በወ/ሕ/አ 539 ሥር የሚወድቁ ከባድ የሰው ግድያን እና በወ/ሕ/አ 671 ሥር የሚወድቁ ከባድ የውንብድና ተግባርን የሚመለከቱ ወንጀሎች ናቸው። ነገር ግን በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ ጉዳዩ ወዲያው በከፍተኛው ፍ/ቤት ቀዳሚ ምርመራ

ማይደረግ እንዲታይ እንዲደረግ ከፍተኛው ፍ/ቤት ሊወስንና የጉዳዩ መታየት በቀጥታ ሊቀጥል ይችላል። ከላይ በተጠቀሱት በከፍተኛው ፍ/ቤት ከሚታዩት ጉዳዮች ውጪ በዚሁ በከፍተኛው ፍ/ቤት ሥልጣን ሥር ብቻ በሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮች ላይ በወ/መ/ሕ/ሥ/ቁ. 38/ለ መሠረት በዐቃቤ ሕግ ውሣኔ ቀዳሚ ምርመራም ሊደረግ ይችላል። በመሆኑም ቀዳሚ ምርመራ መደረግ ያለበት በሁለቱ ዘርፍ ተለይተው በተቀመጡት ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው።

ቀዳሚ ምርመራ የሚደረገው በወረዳ ፍ/ቤት ወይም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ብቻ ነው። በሌሎች ፍ/ቤቶች ሊከናወን አይችልም። ቀዳሚ ምርመራው የሚደረገውም በከፍተኛ ፍ/ቤት ሥልጣን ሥር በሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው።

ቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት ተከሣሹ ና ዐቃቤ ሕግ እንደቀረቡ የተከሣሹ ማንነት ተረጋግጦ ሂደቱ መጀመር አለበት። በቅድሚያ ፍ/ቤቱ ለተከሣሹ ቀዳሚ ምርመራው የሚከናወነው ማስረጃ መዝግቦ ለማቆየት ብቻ እንደሆነና በዐቃቤ ሕግ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ክስ ከቀረበ የተከሣሹ ነፃ መሆን ወይም ጥፋተኛነት የሚረጋገጠው በዚያው ሥልጣን ባለው የከፍተኛው ፍ/ቤት መሆኑን መግለፅ አለበት።

ለተከሣሹ የቀዳሚው ምርመራ ዓላማ በፍ/ቤቱ ከተነገረ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩን በመክፈት ምሥክሮቹ የሚያስረዱትን ገልጾ ምስክሮቹን አቅርቦ ማሰማት አለበት። ተከሣሹ ወይም ጠበቃው መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል። ዐቃቤ ሕግም ድጋሚ ጥያቄውን ማቅረብ ይችላል። ጽ/ቤቱም የሚጣራ ነጥብ ካገኘ የማጣሪያ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል። የቀዳሚ ምርመራው ፍ/ቤት ለትክክለኛ ፍትሕ አሠጣጥ ወደ ፊት ያስፈልጋል ብሎ ካመነ በዐቃቤ ሕግ ባይቆጠሩም በማናቸውም ጊዜ ማንኛውንም ሌላ ምስክር አስቀርቦ መስማት ይችላል።

የዐቃቤ ሕግ ምሥክሮች ከተሰሙ በኋላ ፍ/ቤቱ ተከሣሹን ስለ ክሱ ምላሽ ለመስጠት ፍላጐት እንዳለው ማረጋገጥ አለበት። ቃሉን በመስጠት እንደማይገደድና ቃሉን ከሰጠ ግን ተመዝግቦ በማስረጃነት ወደ ፊት በዐቃቤ ሕግ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ሊቀርብ እንደሚችል ለተከሣሹ ሊነግር ይገባል። ይህ ሁሉ ከተነገረ በኋላ ተከሣሹ ቃሉን ለመስጠ ት ከፈለገ ተመዝግቦ ከተነበበለት በኋላ በፍ/ቤቱ ተፈርሞበት የመዝገቡ አካል ይሆናል።

ተከሣሹ ወደፊት ጉዳዩ በከፍተኛው ፍ/ቤት ሲታይ ለማቅረብ የሚፈልጋቸውን ምሥክሮች እስከነአድራሻቸው ለቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት ማስመዝገብ አለበት፡፡ የሕጉ ዓላማ የሚሆነው በተጨባጭ በወቅቱ ስለ ጉዳዩ ያውቃሉ የሚባሉ ምሥክሮች ካሉ ተለይተው ታውቀው ያለ አግባብ ሀሰተኛ ምሥክር የማቅረብ አሠራርን ለመከላከል ነው፡፡ ይህ ከሆነ ምን ጊዜም ትኩረት ተሠጥቶት ሊተገበር ይገባል፡፡ ለተከሣሹም ማስረጃ እንዲሰማ ተደርጐ እንዳይጠፉ ለምን ተመሣሣይ ጥበቃ አይደረግም የሚል ጥያቄ መነሣት አለበት፡፡ ረቂቁ ሕግ ተከሣሹ ከፊለገ የራሱንም ምሥክሮች አቅርቦ እንዲሰሙ ማድረግ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህ ፍትሃዊ ነው፡፡ ጥበቃው ለሁለቱም ወገን መሆን አለበት፡፡ ዐቃቤ ሕግ አስቀድሞ ስለምሥክሮቹ አውቆ ሌሎች ማስረጃዎችን ያፈላልጋል ብሎ ተከሣሹ ከሰጋ የሚያስገድደው ስለማይኖር ምሥክሮቹን እንዲያሰማ ዕድል መስጠቱ ተገቢ ነው፡፡

በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት የመሠከሩ ምሥክሮች ወደፊት በከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩ ሲሰማ መቅረብ አለባቸው፡፡ ቀደም ብለው ቃላቸውን እንዲሰጡ የሚደረገው ሕጉ ከባድ ብሎ በገመታቸው ጉዳዮች ላይ ማስረጃ እንዳይጠፋ ለጥንቃቄ ብቻ ነው፡፡ ምሥክሮቹ ካልተገኙ ቀደም ብለው የሰጡት ቃል በማስረጃነት ይቀርባል፡፡ የምሥክሮቹን መቅረብ ለማረጋገጥ ወደፊት ጉዳዩ ሲታይ ለመቅረብ ለራሣቸው ዋስትና ፍ/ቤቱ በሚወስነው የገንዘብ መጠን መሠረት መፈረም አለባቸው፡፡ ለመፈረም ፍቃደኛ ያልሆነ ሰው በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል፡፡ ምሥክሩ ከፈረመ በኋላ ቢጠፋና ቢገኝ ጉዳዩ የሚታይበት ጊዜ ተነግሮት ሆነ ብሎ መጥፋቱን ለማረጋገጥ ከባድ ነው፡፡ ዋስትናው ግዴታ ቢፈረምም አፈፃፀሙ አስቸጋሪ ነው፡፡ ለዚህ ይመስላል ከረቂቁ ሕግ ውስጥ ድንጋጌው እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

ጥያቄ ሊያስነሣ የሚችለው ነጥብ ዐቃቤ ሕግ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ክስ አዘጋጅቶ ካቀረበ በኋላ ቀዳሚ ምርመራ ሊደረግ የመቻሉ ጉዳይ ነው፡፡ በሕጉ ላይ በግልፅ ሰፍሮ የሚገኝ ነገር የለም፡፡ ይህ በሌለበት ሁኔታ እና ቀዳሚ ምርመራ ማድረግ ካለው ጠቀሜታ አንፃር መከልከሉ ተገቢ አይመስልም፡፡

ሌላ ሊያወዛግብ የሚችለው የሕጉ ክፍል ለቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት ክሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት እስኪታይ ድረስ ተከሣሹ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ለማዘዝ የመቻል ሥልጣን ነው፡፡ ተከሣሹ በዚህ መልኩ እንዲቆይ በፍ/ቤቱ ከታዘዘ በኋላ በጊዜ ቀጠሮ መልክ ቆይታው በየ14 ቀኑ መታየት አለበት ወይስ ላልተወሰነ ጊዜ በማረፊያ ቤት

ይቆያል በሕጉ ላይ በግልፅ የተመለከተ ነገር የለም። በየ14 ቀኑ በፍ/ቤቱ ክትትል ሊደረግ ይገባል። ይህ ካልተደረገ እና በአፋጣኝ በዐቃቤ ሕግ ክስ ካልቀረበ ተከሣሹ በማረፊያ ቤት ተረስቶ ለረዥም ጊዜ ያለ አግባብ ሊታሰር ይችላል። ይህ ድንጋጌ ከረቂቁ ሕግ ውስጥ እንዳይገባ የተደረገ በመሆኑ ለወደፊት ችግሩ ሊወገድ ይችላል።

በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት ማስረጃ ተሠምቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ግልባጩ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ሬጅስትራር ተላልፎ ጉዳዩ እዚያው እንዲሰማ መታዘዝ አለበት። ዐቃቤ ሕግና ተከሣሹ ግልባጩን ማግኘት የሚችሉት ከከፍተኛው ፍ/ቤት ሬጅስትራር ጽ/ቤት ነው።

በመሆኑም ቀዳሚ ምርመራ መደረጉ ማስረጃ እንዳይጠፋ ትልቅ ጠቀሜታ ስላለው ሊተገበር ይገባል። በሕጉ ዙሪያ ያሉ ችግሮችም በሚገባ ተለይተው ሊሻሻሉ ይገባል።

የመወያያ ነጥቦች፣

1. ቀዳሚ ምርመራ ምንድነው ?

2. ቀዳሚ ምርመራ ምን ጠቀሜታ አለው ?

3. በቀዳሚ ምርመራ ሂደት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ምንድናቸው ?

6. በዐቃቢ ሕግ ክስ የማይቀርብበት ሁኔታ እና የክስ አመሠራረት

የሚጠበቁ ውጤቶች

በዚህ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ ላይ ሠልጣኞች፦

- **ዐቃቤ ሕግ ክስ ላለማቅረብ የሚወስንባቸውን ሁኔታዎች ተረድተው ይተገብራሉ፣**
- **በዐቃቤ ሕግ ክስ እንዴት እንደሚዘጋጅ እና ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት እንደሚቀርብ አውቀው በሥራ ላይ ያውላሉ፤**

ዐቃቤ ሕግ ወንጀል ተፈፀመ ተብሎ የፖሊስ ምርመራ መዝገብ በደረሰው ጊዜ ሁሉ ለፍ/ቤት ክስ አያቀርብም። እነዚህ ዐቃቤ ሕግ ክስ የማያቀረብባቸው ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ በቅድሚያ ይታያል። ዐቃቤ ሕግ ክስ ለማቅረብ በሚወስን ጊዜም ቢሆን በምን መልኩ ክሱ ተዘጋጅቶ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት በመቀጠል ይብራራል።

በወንጀል የግል ክስ ማቅረብ በሕጉ ላይ የተመለከተ ቢሆንም ስለማይተገበርና በአለም ላይ ቦታ እያጣ የመጣ አሠራር በመሆኑ አልተካተተም። ከረቂቁ ሕግ ውስጥም ሙሉ ለሙሉ እንዲወጣ የተደረገ ነው።

6.1. በዐ/ሕግ ክስ የማይቀርብባቸው ሁኔታዎች

ዐቃቤ ሕግ የፖሊስ ምርመራ መዝገብ ተፈፀመ በተባለ ወንጀል ላይ ከተጣራ በኋላ ቢደርሰውም የወንጀል ክስ ለፍ/ቤት ከማቅረቡ በፊት ሕጉ ክስ ማቅረብን የሚከለክልባቸውን ሁኔታዎች መኖራቸውን በሚገባ ሣያጣራ ክስ ማዘጋጀት ና ለፍ/ቤት ማቅረብ የለበትም። ክስ ማቅረብ የመጨረሻ አማራጭ ነው መሆን ያለበት።

ዐቃቤ ሕግ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ እንደደረሰው በበቂ ሁኔታ ያልተጣሩ ነገሮች ካጋጠሙት መዝገቡን መልሶ ለተጨማሪ ምርመራ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.38/ሕ መሠረት

መመለስ አለበት። ክስ ለማቅረብ የሚያጠራጥር ነገር ካጋጠመ የበላይ ዐቃቤ ሕግ መመሪያ እንዲሰጥበት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 41 መሠረትም መተላለፍ አለበት።

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 39 ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በዐቃቤ ሕግ የፖሊስ የምርመራ መዝገብን መዝጋት አለበት። እነዚህም ክስተቶች የተከሣሹ መሞት፣ የዕድሜው ከዘጠኝ ዓመት በታች መሆን፣ በዓለም አቀፍ ሕግ የዲኘሎማቲክ ከለላ መኖር እና በልዩ ሕግ መብት የተሰጠው መሆን ናቸው።

በዐቃቤ ሕግ ክስ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሌሎች ምክንያቶች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 42 ሥር ተዘርዝረዋል። ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ ማስረጃ ከሌለ ክስ መቅረብ የለበትም። ማስረጃው መመዘን ያለበት ጥፋተኛ ለማስደረግ ከማስቻሉ አንፃር ነው። አንድን ወንጀል ለማቋቋም ከሚያስፈልጉት ወሣኝ ነገሮች አንዱ የሆነው የፍሬ ነገር ሁኔታ መኖር ሣይረጋገጥ በምንም ዓይነት ሁኔታ ክስ መቅረብ የለበትም። ለምሣሌ ምስክሮች ለፖሊስ የሰጡት ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭ ከሆነ ክስ ቀርቦ ፍ/ቤትም ቢቀርቡ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ መገመት ይቻላል። ዐቃቤ ሕግ በጥንቃቄ በፖሊስ የምርመራ መዛግብት ውስጥ የሚገኙ ማስረጃዎችን አንዱን ከሌላው ጋር እያነፃፀረ በመመዘን ገለልተኛ በሆነ ሁኔታ ተመልክቶ ክስ ለፍ/ቤት ቢቀርብ ውጤቱ ምን ለሆን እንደሚችል በማገናዘብ መወሰን አለበት። የሕጉ አቀራረፅ ምንም ችግር የሌለበት ሆኖ ሣለ በረቂቁ ሕግ ላይ ጥፋተኛ ለማድረግ የሚለው ሀረግ እንዲወጣ መደረጉ ተገቢነት የለውም። ጥብቅ መሥፈርትን ያስቀመጠው ሕግ እያለ እንኳን ሣይጣራ ክስ ሲቀርብ ይስተዋላል። የባሰ የበለጠ የላላ መሥፈርት ማስቀመጡ በበቂ ሁኔታ ያልተጣሩ ክሶች ለፍ/ቤት እንዲቀርቡ በር የሚከፍት በመሆኑ ረቂቁ ሕግ ሊስተካከል ይገባል። የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮም የሚሳየው ጥፋተኝነትን ለማረጋገጥ በቂ ማስረጃ ከሌለ ክስ መቅረብ እንደሌለበት ነው።

የተከሰሰውን ሰው ለማግኘት የማይቻል ከሆነ ና ጉዳዩም በሌለበት ሊታይ ካልቻለ ክስ ማቅረብ ትርጉም አይኖረውም። በተለይ በዐቃቤ ሕግ በወቅቱ ክስ ተዘጋጅቶ ሣይቀርብ ጊዜ ካለፈ ክስ ከመቅረቡ በፊት በቅድሚያ የተከሣሹ መኖር መጣራት አለበት። ክሱ ከቀረበ በኋላ ፍ/ቤት ያፈላልገው በሚል ሂሣብ ክሱ ከቀረበ ትርፉ ያለ አግባብ የራሱም የዐቃቤ ሕግን ጨምሮ የሕዝብና የመንግሥት ጊዜ ና ሀብት ያለ አግባብ እንዲባክን

ማድረግ ነው። በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ ክስ ከማቅረቡ በፊት ተከሣሹ ሊገኝ መቻል አለመቻሉንና ጉዳዩም ተከሣሽ በሌለበት ሊታይ መቻሉን ማረጋገጥ አለበት።

በይርጋ በታገደ ወይም ለተፈፀመው ወንጀል ምህረት (amnesty) ተደርጉ እንደሆነም ክስ ማቅረብ አይቻልም። በህገ መንግስቱ አንቀፅ 28/1 መሠረት ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በሰው ልጅ ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች፤ የሰው ዘር ማጠፋት፣ ያለ ፍርድ የሞት ቅጣት ዕርምጃ የሚወስድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም። በሕግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሣኔዎች በምህረት ወይም በይቅርታ አይታለፍም። ይቅርታ (pardon) በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ የሚመጣ በመሆኑ ከክስ ማቅረብ ጋር በቀጥታ ግንኙነት የለውም።

ከላይ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጪ ያሉት በሙሉ ቀደም ብሎ በሕግ የተሻሩ ናቸው። በአስፈፃሚው ትዕዛዝ ክስን የማቋረጥ አሠራር የዐቃቤ ሕግን ነፃነት ለማስጠበቅ በአዋጅ ቁጥር 39/85 እንዲሻር ተደርጓል።

ዐቃቤ ሕግ በማናቸውም ምክንያት መዝገብ ሲዘጋ ለበላይ ዐቃቤ ሕግ፣ ለፖሊስና ለተበዳይ ማሣወቅ እንዳለበት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 39/4 እና 43/2 ሥር ተደንግጉ ስለሚገኝ ሁልጊዜ መተግበር አለበት። ይህ ግልፅነተ ና ተጠያቂነትን ለማስፈን ወሣኝ አሠራር በመሆኑ ሊታለፍ አይገባም። በተለይ ለተበዳይ ማሣወቁ ቅር ከተሰኙ ለበላይ ዐቃቤ ሕግ አቤቱታውን በማቅረብ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ሊያስደርግ ስለሚችል ማስተላለፍ አለበት። እራሱ የተበደለ ሰው ቀርቦ እስኪጠየቅ መጠበቅ የለበትም። በፖሊስ አማካኝነት ወይም በቀጥታ በአድራሻው ለተበደለው ወገን የዐቃቤ ሕግ ውሣኔ ሊገለፅለት ይገባል። እስከ መጨረሻው የዐቃቤ ሕግ ኃላፊ ድረስ በተዋረድ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ተገልጋዮች ቅሬታቸውን እንዲያቀርቡ የሚያስችል ምቹ አሠራር መዘርጋት አለበት።

6.2. ክስን ማቅረብ

ዐቃቤ ሕግ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 38/ሀ እና 40 መሠረት ክስ ለማቅረብ የወሰነ እንደሆነ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. ከ108-122 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ክሱን አዘጋጅቶ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ አለበት። የወንጀል ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣኑ የሌለው ፍ/ቤት ክሱ ከቀረበለት መቀበል የለበትም። ለከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበን ጉዳይ መመለስ የማይችለው ወንጀሉ በወ/ሕ/አ 665 ሥር የሚወድቀውን ስርቆትን የተመለከተ እንደሆነ ነው። ይህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥመው ከፍተኛው ፍ/ቤት ዝም ብሎ ጉዳዩን ማስተናገድ አለበት።

ከሥልጣን ጋር ተያይዞ የሚያጋጥመው ሌላው ችግር የተወሰኑ ወንጀሎች በአንዱ ፍ/ቤት ሥልጣን ክልል ሥር ሌሎቹ ደግሞ በሌላ ፍ/ቤት ሥልጣን ክልል ስር የሚወድቁ ሲሆን በምን ዓይነት ሁኔታ መስተናገድ አለባቸው የሚለው ነው። ለምሣሌ በወ/ሕ/አ 635 ስር በስርቆት የተከሰሰ ሰው በተጨማሪ በደንብ መተላለፍ በወ/ሕ/አ 309 መሠረት የሚያስጠይቀውን ስለት ነገር ወይም በወ/ሕ/አ 854 ስር የሚያስጠይቀውን አጠራጣሪ ነገር ይዞ ቢገኝ ክሶቹ የት መቅረብ አለባቸው የሚለው ሊያወዛግብ ይችላል። ለምሳሌ በአዲስ አበባ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን የመመልከት ሥልጣን የተሰጠው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው። የከተማው ፍ/ቤት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የበታች ሊባል የሚችል አይደለም። ከከተማው ፍ/ቤት ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በይግባኝ የሚቀርብ ጉዳይ የለም። በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 109/3 መሠረት የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ወንጀሎቹን ጠቅልሎ ለማየት ሥልጣን ያለው የበላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን እንዲመለከት ነው የሚደነግገው። በክልልም ቢሆን የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በወረዳ ፍ/ቤቶችና የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ካላቸው በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት መሀከል ሊከሰት ይችላል። አሁን ያለውም ሕግ ሆነ ረቂቁ ሕግ ለዚህ ግልፅ ምላሽ የላቸውም።

ዐቃቤ ሕግ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ከደረሰው በኋላ በ15 ቀን ውስጥ ክሱን አዘጋጅቶ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ አለበት። የክሱ ይዘት ሕጉ ያስቀመጠውን ድንጋጌና ፎርም መከተል አለበት። የክሱ ይዘት ሕጉ ያስቀመጠውን ድንጋጌና ፎርም መከተል አለበት። ከይዘቱ ጋር ተያይዞ የሚነሣው አንዱ ችግር ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 111/1/ሐ ሥር የተጠቀሰው ጊዜ የሚለው ቃል ነው። አንዳንዶች ጊዜ ሰዓት፣ ቀን፣ ወርና ዓመትን የሚያጠቃልል ነው። እነዚህ የጊዜ ክፍፍሎች እያንዳንዳቸው በክሱ ላይ

ካልተዘረዘሩ ክሱ ተቀባይነት ለኖረው አይገባም። የተከሣሹን የመከላከል መብት ያጣብባል። ፍ/ቤት ውድቅ ሊያደርገው ይገባል የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ።

በሌላ በኩል የሚነሣው ክርክር ሕጉ የሚለው ጊዜ ነው። ጊዜ ደግሞ በተለያየ መልክ ሊገለፅ ይችላል። እያንዳንዱን የጊዜ ክፍልፋይ የሚቻል ሆኖ ማስቀመጥ ከተቻለ ጥሩ ነው። ነገር ግን ሰዓትና ቀን አልተጠቀሰም ብሎ ከወዲሁ ክሱን ውድቅ ማድረግ ተገቢ አይደለም። ጊዜ ተሟልቶ ባለመጠቀሱ ብቻ ክሱ ከወዲሁ በዚህ ምክንያት ብቻ ውድቅ ሊሆን አይገባም። እያንዳንዱ ጉዳይ ክሱን ለማስረዳት ከቀረበው ማስረጃ አንፃር መታየት አለበት የሚል ክርክር ይቀርባል።

በማኅበራዊ ህይወት ውስጥ የሚያጋጥሙ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ሁኔታውን ለማሣየት ያክል አንድ አባት የሦስት ዓመት ህፃን ልጁን ለማሣደግ ከባለቤቱ ጋር በፍ/ቤት ሲፋታ ተረክቦ እቤቱ ከወሰዳት በኋላ በመደብደብ አካሏ ላይ ከፍተኛ ጊዳት ቢያደርስና ከወራት ቆይታ በኋላ ጉዳዩ ተደርሶበት ሲከሰስ ተበዳይዋ ህፃን ሰዓቱን፣ ቀንና ወሩን አስታውሣ መግለፅ ብትቸገር ጉዳዩ እንዴት መስተናገድ አለበት የሚለው ሊያነጋግር ይችላል። ተበዳይዋ ህፃን በደሉን ያደረሰባት አባቷ መሆኑን ካስረዳችና ጊዜውን ግን ካላስታወሰች በዚህ ምክንያት ብቻ ውድቅ ማድረግ ኢፍትሃዊ ነው የሚሆነው። ዐቃቤ ሕግ ክሱ ላይ በፖሊስምርመራ ጊዜ ሊታወቅ ያልቻለን ጊዜ ሊጠቅስ አይችልም። በእንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች ሰዓቱ ቀነ ፡ና ወሩም ባለመጠቀሱ ብቻ የተከሣሹ መብት ይጣበባል ማለት አስቸጋሪ ነው። በዐ/ህግ ወንጀል መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሣሹ ሕፃኗን በአግባቡ ይዞ ይንከባከብ እንደነበረ ማስረዳት አለበት። በደሉ በሌላ ሰው ደረሰ የሚልም ከሆነ ይህንን ማረጋገጥ አለበት። ኃላፊነቱ የራሱ ነው። የጊዜው ክፍልፋይ አልታወቀም በሚል ምክንያት ብቻ ክሱ ውድቅ ሊሆን ፈፅሞ አይገባም። እንደነገሩ ሁኔታ የቀረበውን ክስ ከሕጉና ከማስረጃው አንፃር መመዘን አለበት። በረቂቁ ሕግ ላይም የሕጉ አቀራረፅ ተመሣሣይ ነው።

በወ/ሕ/አ 23 መሠረት አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው። እነዚህ ሶስት መሠረታዊ መስፈርቶች በክሱ ላይ ተገልፀው መመልከት እንዳለባቸው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 111 ስር ተደንግጓል። ይህንን ለይቶ አብራርቶ ማስቀመጥ እንደቀላል የሚታይ ነገር አይደለም። ዐቃቤ ሕግ ክስ ከማቅረቡ በፊት ተጣሰ የተባለ

የወንጀል ሕግ ድንጋጌ መኖሩን እና የወንጀሉን ማቋቋሚያ መስፈርቶች የአዕምሮ ሁኔታና ግዙፋዊ ተግባራትን መለየት አለበት። በዚህ መልኩ በጥንቃቄ ክስ አዘጋጅቶ ማቅረብ ሁልጊዜ ቀላል አይደለም። አይገባም። እንደነገሩ ሁኔታ የቀረበውን ክስ ከሕጉና ከማስረጃው አንፃር መመዘን አለበት። በረቂቁ ሕግ ላይም የሕጉ አቀራረፅ ተመሣሣይ ነው።

አንድ ሰው ሌላውን በጥፊ ቢመታውና በአካሉ ላይ ፊቱ ከመቅላቱ ውጪ ምንም ጉዳት ባይደርስ ክሱ መቅረብ ያለበት በወ/ሕ/አ 560/1 መሠረት በእጅ ዕልፈት ነው ወይስ በወ/ሕ/አ 840 መሠረት በደንብ መተላለፍ ሊያወዛግብ ይችላል። በተመሣሣይ በወ/ሕ/አ 665 ሥር መውደቅ ያለበት የስርቆት ተግባርና በወ/ሕ/አ 852 መሸፈን ያለበት ቀላል ስርቆት ልዩነት በተጨባጭ አንዳንድ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ለመለየት አስቸጋሪ ነው። እንደ ነገሩ ሁኔታ በአግባቡ እየታየ ክስ መቅረብ አለበት።

ክሱ ሲዘጋጅ ስህተቶች የተሠሩ እንደሆነ ዋጋ አያሰጡትም። ነገር ግን ስህተቱ መሠረታዊ ከሆነ ወይም ተከሣሹ ሊያሣስት የሚችል መሆኑ ከታመነበት ክሱ እንዲሻሻል መደረግ አለበት። ክስን ቀላል አንቀፅን ወደ ከባድ ቀይሮ ለማሻሻል የሚከለክል ሕግ የለም። ስህተት እስከተፈፀመበት ድረስ መስተካከል አለበት። በአግባቡ ምክንያት ለሚፈጠሩ አነስተኛ ስህተቶች ተብሎ ክሱ እንደገና መሻሻሉ ተገቢ አይመስልም። ዐቃቤ ሕግ ና ተከሣሽ ወይም ጠበቃው ከተማመኑ በቀላሉ በችሎት በዐቃቤ ሕግ ሊስተካከሉ የሚችሉ ግድፈቶች መታረም አለባቸው። ክስ ስህተት በተገኘ ጊዜ ሁሉ መስተካከል አለበት። በቀላል መስተካከል የሚችል ጉዳዮች አዲስ ክስ እንደገና ይዘጋጅ ማለት ምክንያታዋ አይመስልም። ጠቃሚው ነገር ዐቃቤ ሕግ ክሱን አዘጋጅቶ ሲያቀርብ በተቻለ መጠን ስህተቶች እንዳይፈጠሩ መጠንቀቅ መሆን አለበት። ክሱ በተስተካከለ ወይም አዲስ ክስ በተጨመረ ቁጥር ለተከሣሹ ተነቦለት እንዲረዳው መደረግ አለበት። የተለየ መቃወሚያ ካለ ወይም መታመኑና መካዱ በድጋሚ መረጋገጥ አለበት። ምክንያቱም በክሱ ላይ የተደረጉትን ለውጦች ተከትሎ ተከሣሹ የተለየ መቃወሚያ ሊያቀርብ ይችላል።

ከዐቃቤ ሕግ ክስ አቀራረብ ጋር ተያይዞ ሣይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ሌላው ነጥብ ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሕግ አንቀፅ ጉዳይ ነው። ነገሩን በምሣሌ ለማስረዳት በወ/ሕ/አ 628/ሀ መሠረት ክስ የሚቀርበው በወ/ሕ/አ 620 እስከ 627

የተመለቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ተፈፅሞ እርግዝና ከተከተለ እና በእነዚህ በቀጥታ በተጣሱት ድንጋጌዎች ውስጥ የተቀመጠው ቅጣት ከወ/ሕ/አ 628/ሀ ካነሰ ነው። የ16 ዓመት ልጅ ተገዳ ብትደፈር ተገቢነት የሚኖረው የሕጉ አንቀፅ 620/2/ሀ ነው። ይህችው ህፃን ሣትገደድ የግብረሥጋ ግንኙነት ብትፈጽም ወንጀሉ የሚወድቀው በወ/ሕ/አ 626/1 ሥር ነው። በአጋጣሚ ህፃኗ ለእርግዝና ብትዳረግ ተገቢነት የሚኖረው የበለጠ ቅጣት ከሁለት የድንጋጌዎች በላይ የሚያስቀጣ የወ/ሕ/አ 628/ሀ ነው። ክስ ሲቀርብ የወ/ሕ/አ 626/2/ሀ እና 628/ሀ ወይም 626/1 እና 628/ሀ ተብሎ ተጣምሮ ተለይቶ መቅረብ መቻል አለበት።

ግልፅ ብሎ ከላይ በተመለከተው መልክ ክሱ የሚቀርብ ከሆነ ዐቃቤ ሕግ እርግዝናውን ማረጋገጥ እንኳን ቢያቅተው አንቀፅ 628/ሀ ወደምን መቀየር እንዳለበት ያረጋግጣል። ከዚህ ሌላ በዋነኝነት አንቀፅ 628/ሀ የመሳሰሉ ድንጋጌዎች እራሣሳቸው ለብቻቸው የሚቆሙ አይደሉም። የወንጀል ተግባሩ በዋነኝነት የሚወድቀው በሌላ የሕግ አንቀፅ ስር ነው። ከዚህ የሕጉ ድንጋጌ ላይ ሌላ ተጨማሪ ሁኔታ ሲያጋጥም ነው ቅጣቱ ከሌላ የሕጉ ድንጋጌ አንፃር መታየት ያለበት። ክሱ ለዐቃቤ ሕግ፣ ለተከሣሹና ለፍ/ቤቱ ግልፅ መሆን አለበት። ጥፋተኛነትን ለማረጋገጥ ከማገዙ በተጨማሪ በቅጣት ጊዜም አስገድዶ ያስረገዘ እና ሣያስገድድ ያስረገዘ በአንድ ዓይነት መታየት የለባቸውም። ሕጉ ሆን ብሎ ነው ለያይቶ ያስቀመጣቸው፤ ወንጀልን የሚያቋቁሙ ድንጋጌዎች በሚገባ መለየት አለባቸው።

አንድን ተግባር ወንጀል አድርጐ ለማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሁሉ ከአንድ በላይ የሕጉ ድንጋጌዎች መጠቀስ አለባቸው፤ ሊጠቀሱ ይገባል። ለምሣሌ ሠራተኛ ስርቆት ከፈፀመ የስርቆት ወንጀልን ምንነት ከሚደነግገው የወ/ሕ/አ 665/1 ጋር ተጣምሮ 669/2/መ መጠቀስ አለበት። መምህር 13 ዓመት ያልሞላትን ተማሪውን ቢደፍርና ከባድ አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ ጉዳት ቢያደርስባት በወ/ሕ/አ 627/1፣ 4/ሀ እና 5 ስር ተጠቃሎ መከሰስ አለበት። የማክበጃ ምክንያቶች ሲኖሩ በቅጣት ጊዜ ይታያሉ የሚለው አስተሳሰብ አሣማኝ አይደለም። ተከሣሹ በህፃኗ ላይ በደሉ ደረሰ ቢባል እንኳን አስቀድሞ አውቆት ጉዳቱ ቀላልና ከባድ መሆን አለመሆኑ ላይ አስፈላጊውን ክርክር ማቅረብ አለበት። ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ ወደኋላ ተመልሶ እንደገና ዐቃቤ ሕግ በፊት ክሱ ላይ ያልተጠቀሰውን የሕግ አንቀፅ 627/5 ጠቅሶ ከባድ ጉዳት ነው የዕድሜ ልክ ፅኑ እስር ይወስን ብሎ ሲያመለክት ተከሣሹ ያላሰበው ስለሚሆን

ከባድ አይደለም ብሎ ሊከራከር ይችላል። ፍ/ቤቱ ወደ ኋላ ተመልሶ እንደገና ማስረጃ ለመስማት የሚፈቅድለት ሕግ የለም። የሂደቱን ተገማችነት ለማረጋገጥ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ሲያዘጋጅ አንድን ተግባር ወንጀል ያደረጉትን የሕጉን ድንጋጌዎች በጥንቃቄ አገናዝቦ ተገቢነት ና ተያያዥነት ያላቸውን ከአንድም በላይ ቢሆን ጠቅሶ ግልፅ ክስ ማቅረብ አለበት።

በክሱ ላይ የማስረጃ አጠቃቀስን በተመለከተ የተለያየ አሠራር አለ። ምስክሮች፣ ሠነዶችና ሌሎች ማስረጃዎች ምን እንደሚያስረዱ ለማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ላይ በግልፅ ማስቀመጥ በጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ የተለመደ አሠራር ነው። ይህ በችሎት ሂደት ምስክሩ በቀጥታ ወንጀሉን ሲፈጽም ያየ የዓይን ምስክር ነው ወይስ በተዘዋዋሪ መንገድ ያወቀ የሚለውን ለይቶ ቢያስቀምጥ እራሱ ዐቃቤ ሕግ የችሎቱን ሂደት በቀላሉ ለመምራትና አላስፈላጊ የተደጋገመ የምስክርነት ቃልን ለመለየት ስለሚረዳ ጠ ቀሜታው የጐላ በመሆኑ ሊተገበር ይገባል። በአብዛኛው ግን የማስረጃ ዝርዝር ስር ማስረጃዎችን በቻ በመጥቀስ በግልፅ የሚያስረዱትን ሣያረጋግጡ ማቅረብ የተለመደ ነው።

በረቂቁ ሕግ ላይ ከክስ አቀራረብ ጋር በተያያዘ የተደረገ መሠረታዊ ለውጥ የለም። ከክስ አዘገጃጀትና አቀራረብ ጋር በተያያዘ እያጋጠሙ ያሉና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ከግንዛቤ ውስጥ ገብተው ሕጉ ተሻሽሎ መፅደቅ አለበት።

ስለዚህ ዐቃቤ ሕግ ክስን ማቅረብ የመጨረሻ አማራጭ አድርጐ መውሰድ አለበት። ከክስ በፊት ጉዳዩ ዕልባት ማግኘት ካለበት ይህንን አረጋግጦ መዝገቡ መዘጋት አለበት። ክስ ለማቅረብ ከወሰነም አዘገጃጀቱ ሕጉን ተከትሎ ፍትሐዊ ውሣኔ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ግልፅ የሆነ ክስ መቅረብ አለበት።

የመወያያ ነጥቦች

1. ዐቃቤ ሕግ ክስ አዘጋጅቶ ከማቅረቡ በፊት ሊከተላቸው የሚገቡ ሂደቶች ምንድናቸው ?

2. ብቃት ያላቸውን ክሶች አዘጋጅቶ ለማቅረብ ዐቃቤ ሕግ ምን ዓይነት አሠራሮችን መከተል አለበት?

3. ክስ ላይ ማናቸውም ዓይነት ቀላል ስህተት በተገኘ ቁጥር ተሻሽሎ አዲስ ክስ መቅረብ አለበት ወይስ እንደነገሩ ሁኔታ እየታየ ቀላል ስህተቶች በፍ/ቤቱ እውቅና የተከሣሹ ወይም ጠበቃው አስተያየት ተሰምቶ እዚያው ክሱ ላይ ሊስተካከል ይገባል?

4. ክስን ከቀላል ወደ ከባድ ማሻሻል ሊከለከል ይገባል ወይ?

5. ቅጣት የሚያከብዱ ሁኔታዎች ሲኖሩ በምን መልኩ ክስ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት?

ዋቢ ጽሁፎች

1. Andrew West, Yvon Desdevises et al, *The French Legal System, an Introduction*, (London: Fourmat Publishing, 1993).

2. **ብ/ጄኔራል ታጠቅ ታደሰ፣ *የማስረጃ ሕግ መሠረተ ሃሳቦች*፤ (አዲስ አበባ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መጻህፍት ማዕከል፣ 1ኛ ዕትም፣** 1996).

3. Bryan A. Garner(ed.), *Black's Law Dictionary*, (Washington: West Publishing Co., 8th ed ., 2004).

4. Jerold H. Israel, and Wayne R La Fave, *Criminal Procedure, Constitutional Limitations in anut shell*, (St. Paul: West Publishing Co., 8th ed., 2001).

5. John N. Ferdico, *Criminal Procedure*, (Stamford: Wadsworth Group, 8th ed., 2002).

6. J.W.Ceil Turner, *Kenny's Outlines of Criminal Law*, (New Delhi: Universal Law Publishing Co. Pvt. Ltd., 19thed., Second Indian Reprint, 2004).

7. Marvin Zalman and Larry Siegel, *Key Cases and Comments on Criminal Procedure*, (St. Paul: West Publishing Co., 1994 ed., 1995).

8. Stanley Z Fisher, *Ethiopian Criminal Procedure, a Sourcebook,* (Addis Ababa: the Faculty of Law Haileselassie I University and Oxford University Press, 1969).

9. **ፀሐይ ወዳ፣ *የወንጀል ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች*፣(አዲስ አበባ፣ *1994 ዓ.ም*).**

10. Wayne R. LaFave and Jerold H. Israel, *Criminal Procedure*, (St. Paul: West Publishing Co., 4th ed., 2004).